# ውድ ዐብደላ

ጌርሃርድ ኔህልስ

ይህ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል

የተሻለ መግባባት ይኖር ዘንድ፥ ልብ ወለድ በሆነ መልኩ የቀረበ የደብዳቤ ልውውጥ ነው።

«ዐብደላ» የሚለው ስም በዐረብኛ «የእግዚአብሔር አገልጋይ» ማለት ነው።

ደብዳቤውን የሚጽፈውን የሚጽፈውም ሰው ስም በግሪክ

«በእግዚአብሔር የተወደደ»

ማለት ነው።

# ቁጥር 1

ውድ ዐብደላ፣-

ይህን ደብዳቤ የምጽፍልህ፣ ከአንተ ጋር በመገናኘቴ ምን ያህል ደስ እንደተሰኘሁ ልነግርህ ነው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ አንድ ክርስቲያንና አንድ ሙስሊም የሚገናኙ አይመስልም ነበር። ሆኖም በመካከላችንም ብዙ ተመሳሳይ መሠረቶችን ማግኘት ችለናል። ሁለታችን ተቀራራቢ፣ መልካም ምኞቶችና ተስፋዎች እንዳሉን ለመገንዘብ ችለናል። ተስፋ ያደረግነው ነገር ሲከሰም የሚሜነን የኀዘን ደመናና መሻታችንም እንዲሁ ተመሳሳይነት ያለው ነው። እንዲሁም ደግሞ ሁሉን ቻይ በሆነው አምላክ፣ እርሱ በገለጻቸው ራእዮች፣ በነቢያቶቹ፣ ከሞት በኋላ ባለው ሕይወት፣ በመጨረሻው ፍርድና እርሱን ተከትሎ በሚመጣው ሽልማት በጋራ እናምናለን። ሽልማቱም ላሰብነውና ላደረግነው ሁሉ እንደሆነ እንስትም።

ሁለታችንም ንጹሕ ልብ እንደሌለን መገንዘባችን ደግሞ ለእኔ ትልቅ ትርጉም የሰጠኝ ነጥብ ነው። ኢየሱስ አንድ ጊዜ ንጹሕ ልብ ያላቸው እግዚአብሔርን ለማየት እንደሚችሉ ተናግሮ ነበር (ማቴ. 5፥8)። በተጨማሪም የሚከተለው የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ትዝ ይለኛል፣-

> «እንደሚታዘዙ ልጆች ባለማወቃችሁ አስቀድሞ የኖራችሁበትን ምኞት አትከተሉ። ዳሩ ግን፣ ‹እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ› ተብሎ ስለተጻፈ፣ የጠራችሁ ቅዱስ ስለሆነ፣ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ»
>
> (1 ጴጥ. 1፥14-16)
>
> «ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ! ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና»
>
> (ዕብ. 12፥14)

ሙሉ ለሙሉ ራስን ለእግዚአብሔር የመስጠትና ለእርሱም የመታዘዝ ጉድለት፣ እንዲሁም የዚህ ዓይነት ቅድስና እጦት፣ ከእርሱም ወደ መለየት ትልቅ የኀዘን ሸለቆ ይመራል። ከእግዚአብሔርም ዘንድ አንድ ዓይነት የማዳን መንገድ፣ ቃል ተከፈተ፣ የዚህ ነገር መጨረሻው እኛን ወደ ሲኦል ማውረድ ነው!

በማስተዋልም ሆነ ባለማስተዋል ለዚህ ነገር ያለን ግንዛቤ፣ የሞትን ፍርሃት በእያንዳንዳችን ውስጥ ያስቀምጣል። ቁንጠኞች፣ ደስተኞችና ፍልቅልቅ ሰዎች ልንሆን እንችላለን! የሕይወትንም ምርጥ ጣዕም እያጣጣምን ልንሆን እንችላለን። ይሁን እንጂ፣ ይህ ሁሉ ሊመጣ ካለው ከሞት ፍርሃት የተነሣ ከንቱ ይሆናል።

ብዙዎቹ ሃይማኖቶች መንጻትን የሚያጎሉ ሥርዓቶችን እንደሚለማመዱ ማጤኑ አይመስጥምን? እነዚህ ምሳሌያዊ የነገር ጥላዎች ብቻ ናቸው። በእርግጥ እያንዳንዱ

የማንጻት ሥርዓት፡ መንጻት እንደሚያስፈልገን ያስታውሰናል፡ ምክንያቱም እኛ ንጹሐን አይደለንምና። ይሁን እንጂ ልብ በውኃ በመታጠብ ሊጠራ አይችልም!

ሁለታችንም
«ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት፡ ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደተመደበባቸው»
(ዕብ. 9:27)

እናምናለን። ስለዚህ ሁለታችንም በአንድ ጀልባ ውስጥ መቀመጣችን ግልጽ ነው። እንደማንኛውም ሰው፥ ሁለታችንም በአሳብና በቃል እንዲያውም በሥራችንም ጭምር በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአትን ሠርተናል። ጠፍተናል! ይሁንና ሁለታችንም ከእግዚአብሔር ዘንድ የምንጠብቃቸውና ተስፋ የምናደርጋቸው የተወሰኑ ነገሮች አሉን። ሁለታችንም ትክክል ነው ተብሎ በተነገረን ሃይማኖት እናምናለን።

በርካታ መንፈሳዊ ነገሮችን ብንጋራም ቅሉ፥ በእምነቶቻችን ውስጥ መሠረታዊ የሆኑ ልዩነቶችም ደግሞ አሉ። ይህ ልዩነት ችግር የሚፈጥር ነውን? እንደሚመስለኝ ችግር መፍጠሩ አይቀርም።

በዚህ ነጥብ ላይ ውይይታችን የተለመደው መፍረክረክ የሚያጋጥመው ይመስላል፤ ይህ ቢሆን ግን ይገባልን? በታማኝነት ጉዳዩን በመጋፈጥ፥ እውነቱን በጋራ ለመፈለግ መስማማቱ አይሻልምን? ከሁሉም በላይ ይህ የዘለዓለም ጉዳይ እኮ ነው! የሚመለከተውም እኛን ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔርንም ጭምር ነው። ከሁለት አንዳችን ወደ ሲኦል እየወረድን ግድየለሽ ለመሆን እንደፍራለንን? የምናምነው ነገር ከሕያው እግዚአብሔር የተገለጸና የተረጋገጠ ራእይ እስቃልሆነ ድረስ፥ መጠራጠር አለብን። እጅግ ብዙው ሰው ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን ተከታትሏል። ዳሩ ግን ከእግዚአብሔር ይልቅ በሰው ልንደገፍ ይገባልን? መጽሐፍ ቅዱስ፡-
«በሰው የሚታመን . . . ርጉም ነው»
(ኤር. 17:5) ይላል።

እኛ ከእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል። ግን እውነትን ብናምንና ብንከተል፥ ምን ነገር ሊያስፈራን ይችላል? የእግዚአብሔር እውነት ሊገለጽ ይገባል! እግዚአብሔር ወደተናገረው ነገር እራሳችንን አናቀርብም ማለታችን እራሱ በያዝነው ነገር ዋስትና እንደሌለን የሚያጋልጥ አይደለምን?

አንተን የማውቅህ በመጠኑ ቢሆንም፥ አብረን ቅንነትና ማስተዋል ባለው ፍርድ፥ በዚህ ዓለም ካለው ከማንኛውም ነገር ይልቅ የሚመለከተንን ጉዳይ ወደ ብርሃን እንደምናወጣው እርግጠኛ ነኝ።

ያንተው ቴዎፍሎስ

# ቁጥር 2

ውድ ዐብደላ፡-

ከልብ የመነጨው እውነተኛ ምላሽህን በመጠባበቄ እንዳልተሳሳትሁ አውቄ ነበር። አመሰግናለሁ። ቅንነት ግሩም ነገር እንደሆነ አንተም ትስማማኛለህ። ዳሩ ግን ሰው በቅንነት ሊሳሳት ይችላል! ስለዚህም ዋናው ነገር በቅንነታችን ላይ ሳይሆን፥ ቅን የሆንለት ጉዳይ ላይ ነው። ቅንነት ስሕተትን ወደ እውነት አይለውጥም። ስለዚህም ታማኝነትህን እያደነቅሁ፥ ከጻፍህልኝ ነገር በአንዳንዶቹ ልስማማህ አልችልም። ይህንንም እንድትቀበለኝ በትሕትና እየጠየቅሁ፥ ማብራሪያዎቼን ቀጥዬ አቀርብልሃለሁ።

ዛሬ እንደምናውቀው፥ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኝነት እንዳትቀበል የሚያግድህ ሥሩን የሰደደ ጥርጣሬ እንዳለህ ገልጸሃል። በአንድ በኩል እኔም ይህንን ጠብቄ ነበር። በሌላ ወገን ግን አስደንቆኛል። መልስ በምሰጥህ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስን (ወይም የቁርዓን) «ዘመናዊ» ሂሶችና መላምቶቻቸውን ለጊዜው እንደምናገልል ልነግርህ እፈልጋለሁ። ይልቁንም እስቲ በትክክል ሊረጋገጥ ወደሚችለው ወደ ታሪክ እንመልከት። በመጀመሪያ አንድን አመለካከት ካስቀመጡ በኋላ ለማጠናከሪያ የሚሆኑ አሳቦችን ማቅረብ የተለመደ ነገር ሆኗል! ይህ ተገላቢጦሽ መሆን ይገባው ነበር!

የመጽሐፍ ቅዱስን መበላሸት በተመለከተ፥ አንዳንድ ጥያቄዎች ብጠይቅህ ቅር ይልህ ይሆን? መጽሐፍ ቅዱስን የለወጠው፥ ወይም ያበላሸው ማነው? መጽሐፍ ቅዱስስ የተበላሸው መቼ ነው? የመጀመሪያው ቅጂ የታለ? ወይም የመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ እንደነበር የሚጠቁሙ መረጃዎች የት አሉ? ከእነዚህ ጥያቄዎች መካከል ለአንደኛቸውም እንኳ መልስ ስለሌለ፥ ከዚህ ነጥብ ወደ ሌላው እሻገራለሁ።

ቀጥሎ ያለጥርጥር መመሪያህ የሆነው ቁርዓን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ለመጠየቅ እፈልጋለሁ። ጥያቄውን እኔው ልመልሰው ይሆን?

> «በአላህና ወደ እኛ በተወረደው ቁርዓን፥ ወደ ኢብራሂምም፥ ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም፥ ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም፥ በተወረደው፥ በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት፥ በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት፥ ከእነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን አመንን»
>
> (ሱረቱ አል. በቀራህ 2፡136)

> «በፈለጎቻቸው (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን፥ ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን አስከተልን፤ ኢንጅልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት፥ በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ፥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሣጭ ሲሆን ሰጠነው፥ የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህም ባወረደው

ሕግ ይፍረዱ፤ አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው እነዚያ አመጠኞች እነርሱ ናቸው»

(ሱረቱ አል-ሚኢዳህ 5፥46-47)

«በሉም፡- በዚያ ወደ እኛ በተወረደው፥ ወደ እናንተም በተወረደው አመንን»
(ሱረቱ አል-ዐንከቡት 29፥46)

«ከአንተም በፊት ወደነሱ የምናወርድላቸው የሆኑ ሰዎችን እንጂ ሌላን አልላክንም፤ የማታውቁም ብትሆኑ፥ የመጽሐፉን ባለቤቶች ጠይቁ»
(ሱረቱ አል-አንቢያ 21፥7)

ነገር ለማሳጠር ያህል፥ ይህ በቂ ሊሆን ይችላል። ቁርዓን በማንኛውም መንገድ የመጽሐፍ ቅዱስን ሙሉነት፥ ተአማኒነት፥ መለኮታዊ መሠረትና ሕልውና እንደማይቀናቀን በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ መመልከት እንችላለን። በተጨማሪም የእግዚአብሔርን ቃል በፈቃዱ ሊለውጥ የሚችል ማነው? አሁንም ቁርዓን መልስ ይሰጠናል፡-

«የአላህ ቃላት መለለወጥ የላትም»
(ሱረቱ የኑስ 10፥64)

«የአላህንም ንግግሮች ለዋጭ የለም»
(ሱረቱ አል-አንዓም 6፥34)

የሚከተሉት ሁለት የቁርዓን ምንባቦች መጽሐፍ ቅዱስ እንደተበላሸ አድርገው [illegible] አድርገን እንዳንተረጉም መጠንቀቅ አለብን፡-

«እነዚያም በልቦቻቸው ውስጥ ጥመት ያለባቸው ሰዎች ማሳሳትን ለመፈለግና ትችቱን ለመፈለግ ከእርሱ የተመሳሰለውን ይከታተላሉ»
(ሱራ አሊ-ዒምራን 3፥71)

መጽሐፍ ቅዱስ ከመሐመድ በኋላ ተለውጧል ብሎ ማሰብ ተቀባይነት የሌለው ነገር ነው። በእጃችን ያሉት ወደ 5000 የሚጠጉት የአዲስ ኪዳን ሰነዶች በሙሉ የእያሌ ዓመታት ቀደምትነት አላቸው።

እዚህ ላይ እንደ አት-ታባሪ (በ855 ዓ.ም. የሞተ)፥ አል-ግሃዛሊ (በ1111 ዓ.ም. የሞተ)፥ አል-ቡክሃሪ (በ870 ዓ.ም. የሞተ) በ (ግሪክ) የወንጌል መጽሐፍ ትክክለኛነት እንዳመኑ ጨምረን ለመግለጽ እንችላለን። ላሩ ግን ቁርዓንና ታሪክ አሌ እያሉ፥ ታዲያ ብዙ ሙስሊሞች ለምን መጽሐፍ ቅዱስ ተለውጧል ብለው ያምናሉ? የሚል ጥያቄ ታነሣ ይሆናል። አሁንም እስቲ የራሴን ጥያቄ እኔው ለመልስ፡-

«እብን ቃስም (በ1064 ዓ.ም. የሞተ) የእስፔይንን ደቡባዊ ክፍል ለተወሰነ ጊዜ የከሊፋው ባለሥልጣን በመሆን አስተዳድሯል ... ይህ ሰው በሥነ-መለኮት ውይይቶችም ውስጥ ተሳትፎ አድርጓል ... እስልምናን ደግፎ ከክርስቲያኖችም ጋር ሲከራከር፥ እብን ቃስም ቁርዓን ከወንጌል ጋር ከሚጋጭባቸው ነጥቦች ላይ ደረሰ። አንድ ግልጽ ምሳሌ የሚከተለው የቅራኔ ክፍል ነበር፦

> «አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም»
> (ሱረቱ 4፡157)

«ቁርዓን እውነት መሆን ስላለበት፥» ሲል ተከራከረ እብን ቃስም፥ «ውሸት የሆነው ከቁርዓን ጋር የሚጋጨው የወንጌል ክፍል ነው። ነገር ግን መሐመድ ወንጌልን እንድናከብር ይነግረናል። ስለዚህ አሁን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቲያኖች ወደ ውሸትነት የተቀየረ መሆን አለበት»። ይህ አሳቡ በታሪካዊ ሐቆች ላይ የተመረኮዘ አይደለም። ይልቁንም በግል አመለካከቱና የቁርዓንን እውነተኛነት ለመጠበቅ ባደረገው ጥረቱ የቀረበ ዘገባ ነው። አንድ ጊዜ በዚህ መሥመር መጓዝ ስለጀመረ፥ ይህን የመከሰሻ መንገድ ከማስፋፋት ምንም ሊገታው አልቻለም። እርግጥ፥ ተፋላሚዎችን ለማጥቃት ቀላሉ መንገድ ይመስል ነበር። «የመጽሐፋቸውን ውሸተኛነት ካረጋገጥን፥ ከዚያ ውስጥ የሚያመጧቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች ያጣሉ»። ይህም በመጨረሻው የሚከተለውን የማጠቃለያ ዐረፍተ ነገር ወደ መጻፍ መራው፡-

> «እግዚአብሔር እነርሱን መቃወሚያ ይሆነው ዘንድ ከተወው ክፍል በስተቀር፥ ክርስቲያኖች የተገለጸውን ወንጌላቸውን አጥተውታል»።
> [«በወንጌሉ ለመታመን እንችላለንን?» ከሚለው የጆን ውጅንጋርድ መጽሐፍ የተወሰደ]

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐቀኝነት በጥያቄ ምልክት ውስጥ ገባ። ውድ ዐብደላ፥ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኝነት በተጨማሪ የሚደግፉ በጣም ጠንካራ የከርሰ-ምድር ጥናትና የታሪክ መረጃዎች ሳያቀርብልህ እንኳ በጉዳዩ እንድትፈርድ ለአንተ እተወዋለሁ።

ምናልባት ይህ ደብዳቤ፥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔር ቃልነቱ በልብህና በሕይወትህ ውስጥ የተለየ ቦታ ሊሰጠው እና የሰዎች የመከራከሪያ ነጥቦች ግን በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊመረመሩ እንደሚገባ እንድታስተውል ረድቶህ ይሆናል። ዳሩ ግን በዚህ ደብዳቤ እንደተጠቀሰው፥ እንደዚህ ስላሉት ነገሮች የተወሰነ ግንዛቤ የመጨበጡ ጠቀሜታ የማያጠያይቅ ነው።

የባሕላዊ እምነቶችን መፈራረስ ስንመለከተ፥ ከተለያየ አቅጣጫ የሚሰማህን ጉዳት በትዕግሥት ለመቻል አንተም እንደኔው ዝግጁ እንደሆንክ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህን ለእውነት ስንል ልንቀበለው ይገባናል። ከዚህ የተሻለ ምን ልናደርግ እንችላለን?

ይህ ደብዳቤ በጤና እንደሚደርስህ ተስፋ አደርጋለሁ። እባክህ መልሱን ፈጥነህ ላክልኝ።

እጅግ ከደመቀ ሰላምታ ጋር የምሰናበትህ፥

ያንተው

ቴዎፍሎስ ነኝ።

# ቁጥር 3

ውድ ዐብደላ፥

እናንተ ነብዩ ዒሳ ስለምትሉት ስለ ኢየሱስ ያለህን ግንዛቤ ስላካፈልከኝ በጣም አመሰግንሃለሁ።

እናንተ ካላችሁ፥ ግንዛቤ ጋር በብዙ መንገድ በመለያየታቸው ሳቢያ ስለ እርሱ በሚሰጡት ክርስቲያናዊ አመለካከቶች ላይ ተቃውሞ እንዳለህ ለመረዳት አስችሉኛል።

እነዚህ አመለካከቶች በጣም ጠንካራ በሆኑ መሠረቶች ላይ እንደተመረኮዙ እንድትገነዘብ እፈልጋለሁ። ለዚህም ጉዳይ አእምሮህን ክፍት ለማድረግ ሞክር።

በመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ፥ «ፍጥረታዊ ሰው» ከ «መንፈሳዊ ሰው» በተቃራኒ፥

> «የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስ የሚመራመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም»
>
> (1 ቆሮ. 2፡14)

መንፈሳዊውን ነገር ለመረዳት አለመብቃት፥ የመንፈሳዊ ብርሃን እጦት ውጤት ነው። መንፈሳዊ ነገሮችን መረዳት በልብና በአእምሮ መንፈሳዊ አቋም ላይ ይመሠረታል። መንፈሳዊ ሰው ብቻ፥ ከራሱም፥ ወይም ከሌላው ሰው ፈቃድ በተቃራኒ በእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ውስጥ መሆንና መኖር ይፈልጋል። መንፈሳዊ ሰው በሙሉ ታማኝነት፥ በተከፈተ አእምሮና በመመራመር በእግዚአብሔር ቃልና በሰው ሃይማኖት መካከል ያለውን ልዩነት ይረዳል። ምክንያቱም እርሱ የሚመለከተው መለየት የሚችለውን መለኮታዊ ምልክት ነው። ይህም መለኮታዊ ማገናዘብ በሚችል አእምሮ እንኳ ለመረዳት የሚቻል ነው።

ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በገለጸው ነገር ያምናሉ። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ደራሲነት ምልክት ይዟልና ነው። ይህም የተፈጸመ ትንቢት ነው። እንዲሁም በማያጠራጥሩ ሐረጎች ትንቢቱ ያልያዘለት ነቢይ እውነተኛ ነቢይ እንዳልሆነ ተነግሮናል (ዘዳ. 18፡21፥ 22 እና ኢሳ. 41፡22፥ 23)።

እንደዚሁም በወንጌላት ሁሉ «እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈው»፥ ወይም «ነቢዩ እንዳለው» የሚሉ ሐረጎችን እናገኛለን።

> «እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ፤ እንዲህ ብዬ፤- መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረም፤ መጽሐፍም

እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ። ለኬፋም ታየ፤ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ፤ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል»

(1 ቆሮ. 15፡3-6)

«መጽሐፍ እንደሚል» የሚሉ ቃላት በመቶ ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት ይኖሩ በነበሩ ነቢያት የተጻፈውንና በኢየሱስ የተፈጸመውን ነገር የሚያመለክቱ ናቸው። እነዚህ ነቢያት በገዛ መላምታቸው ሊደርሱባቸው ስለማይችሏቸው በርካታ ክስተቶች ጽፈዋል። ዐቢይ ርዕሳቸውስ ምን ነበር? መሢሑ ኢየሱስ ነበር።

መቼና የት እንደሚገለጽ ተናግረው ነበር፤ ከማን እንደሚወለድና ስሙ ማን እንደሚባልም ገልጸው ነበር። መለኮታዊ ባሕርዩ እንኳ ሳይቀር፥ ካደረጋቸው ነገሮች ብዙው ተተንብየዋል። ይህም እንዴትና ለምን እንደሚሞት በሚናገሩ ትንቢቶች እጅግ ይጎላል። ከእነዚህ ትንቢቶች መካከል ሁለት ወይም ሦስቱ ለብዙዎቹ ይወከላሉ። አንደኛው ዳዊት በ1000 ዓ.ዓ. ተንብዮአል፡-

> «ብዙ ውሾች ከብበውኛልና፤ የክፉተኞች ጉባኤ ያዘኝ፤ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ። አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ እነርሱም አዩኝ፤ ተመለከቱኝም። ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፤ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ»
>
> [መዝ. (22)፡ 16-18]

ነቢዩ ኢሳይያስም በ700 ዓ.ዓ. እንዲህ ብሏል፡-

> «የተናቀ፥ ከሰውም የተጠላ፥ የሕመም ሰው፥ ደዌንም የሚያውቅ ነው፤ ሰውም ፊቱም እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፤ እኛም አላከበርነውም።
>
> «በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕመማችንንም ተሸከሞአል፤ እኛ ግን እንደተመታ፥ በእግዚአብሔርም እንደተቀሠፈ፥ እንደተቸገረም ቆጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደበጎች ተቀበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።
>
> «ተጨነቀ፤ ተሰቃየም፤ አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ፤ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር፤ በአፉም ተንኮል አልተገኘበትም ነበር።
>
> « ... ጻድቅ ባሪያዬም በዕውቀቱ ብዙዎችን ያጸድቃል፤ ኃጢአታቸውንም ይሸከማል። ... እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፤ ስለ ዐመፀኞችም ማለደ»
>
> (ኢሳ. 53)

ማንም ታማኝ ኅሊና ያለው ሰው እንዲህ ያለውን መረጃ ወደጎን ሊተው አይችልም። ይህንን የበለጠ ገሃድ ለማድረግ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በርካታ የዓይን ምስክሮችን ዘገባ ያካትታል፤ የዓይን ምስክሮቹ ዘገባ እውነት ባይሆን ኖሮ፥ ለጊዜው በነበሩት ሰዎች ይወገዝ እንደነበር ግልጽ ነው። ከስቅለቱ ሰባት ሳምንታት ብቻ ከተቆጠሩ በኋላ ለብዙ ሕዝብ የሚከተለውን ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ፥ የኢየሱስ የቅርብ ተከታይ በሆነው በሐዋርያው ጴጥሮስ ላይ፥ በኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁዶች ምን ያደርጉ እንደነበረ መገመት ትችላለህ።

> «የእሥራኤል ሰዎች ሆይ፥ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች፥ በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ፤ እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው ዕውቀቱ ተሰጥቶ በዐመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት። እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፤ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና»
>
> (የሐዋ. 2፡22-24)

ምንም እንኳ አይሁዶች የኢየሱስን መሢሕነት ቢጠራጠሩም፥ በመስቀል ላይ መሞቱን በፍጹም አልካዱም። እነርሱ እዚያው ስለነበሩ መቼም ስለ ነገሩ እውነተኛውን ያውቁ ነበር።

የእግዚአብሔርን ቃል ተአማኒነት ለመደገፍ ሌላ አንድ ተጨማሪ መረጃ ማቅረቡ ሳይሻል አይቀርም። ይኸውም የታሪክ ዘገባ ነው። በእርግጥ የጦርነት ዜናዎችንና የጦር ሜዳ ጀብደኞችን ጉዳይ ለሚዘግቡት የዘመኑ የሮማ የታሪክ ጸሐፊዎች በገጠሪቱ ይሁዳ የተፈጸመው የኢየሱስ ታሪክ ምንም አስተዋጽኦ እንዳልነበረው እንገነዘባለን። ይሁን እንጂ የሮሜ ታላቁ የታሪክ ጸሐፊ ቆርኔሌዎስ ታሲተስ የሚከተለውን ጽፎአል፡- ይህም ሰው የቀድሞይቱ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ ተፃራሪ የነበረ ሰው ነው።

> «ክርስቲያን የሚለው ስም የመጣላቸው በጲላጦስ ዘመን ከተገደለው ከክርስቶስ ነው»

ፍልቪየስ ጆሴፈስ አይሁዳዊ ቢሆንም፥ ስለ እሥራኤል የሮማ የታሪክ ጸሐፊ ሆኖ ሠርቷል። ከኢየሱስ ዘመን በኋላ ብዙም ሳይቆይ የነበረ ሲሆን፥ የሚከተለውን ጽፎአል፡-

> በዚያን ዘመን «ኢየሱስ የሚባል አንድ አዋቂ ሰው ነበረ። ይልቁንም የድንቅ ሥራዎች አድራጊ፥ እውነትን በቅንነት የሚቀበሉ የብዙዎች መምህር ስለነበረ ሰው ነው ለማለት እንኳ አያስደፍርም። ብዙ አይሁዶችንና በርካታ አሕዛቦችንም ወደራሱ ሳበ። እርሱ ክርስቶስ ነበረ። እንዲሁም በዋነኞቻችን ምክር ጲላጦስ ለመስቀል ሞት አሳልፎ በሰጠው ጊዜ፥ በመጀመሪያ የወደዱት ሰዎች አልተዉትም ነበር። ይህም የሆነው በሦስተኛው ቀን እንደገና ስለተገለጸላቸው ነው። ይህም

የሆነው፥ ልክ ቅዱሳን ነቢያት እነዚህንና ሌሎች አሥር ሺህ አስደናቂ ነገሮችን» እንደተነበዩዋቸው ነው።

ለምንድነው በምድር ላይ በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ይህንን መረጃ የሚቀበሉት? ከፍርሃት የተነሣ ይሆን? ወይስ ከኩራት የተነሣ? እነዚህን ሐቆች አለማወቅም ምናልባት ሌላው ምክንያት ሊሆን ይችላል።

መረጃዎቹን እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠበት ምክንያት አለ፡- እርሱ ሊያስተላልፍልን ስለፈለገው መልእክት ምንም ዓይነት ጥርጥር እንዳይኖረን፥ ለእኛ ባደረገልን ነገር ሙሉ ለሙሉ መደገፋችን እንድንገነዘብና፥ እግዚአብሔር ለሽያጭ ላላቀረበው ነገር ክፍያ ለማቅረብ መሞከራችን ከንቱ ጥረት መሆኑን እንድንረዳ ይፈልጋል። ምሕረቱና ጸጋው፥ ይቅርታውና ስርየቱ የማይከፈልባቸው ነፃ ስጦታዎች ናቸው። እነዚህን ነገሮች በማጣታችን ምክንያት፥ እግዚአብሔር እንደ ነፃ ስጦታ ሰጥቶናል። ይቅርታውና ስርየቱ በራስ ጥረት የሚገኙ ነገሮች አይደሉም!

ማድረግ የሚገባን ብቸኛው ነገር እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለኃጢአታችን በመስቀል የከፈለውን ክፍያ በትሕትናና በእውነተኛ ጸጸት ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን ብቻ ነው። ከዚህም በኋላ የደስታ ሕይወት ይከተላል። የእርሱን ስጦታ በትሕትናና በጸጸት ከተቀበልን፥ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን! እንዲሁም ከዚህ ወዴት እንደምንሄድ እናውቃለን። ሕይወታችን ላደረገልን ነገር በምስጋና ይሞላል። ይህም በተለወጠ ሕይወት ውስጥ በመልካም ሥራዎች ይገለጻል። የመልካም ምግባራችን ምክንያት መንግሥተ-ሰማይን ለመውረስ ስንል ሳይሆን፥ ስላደረገልን ነገርና ስለ እርሱነቱ እግዚአብሔርን ስለምናፈቅረው ነው።

> «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፤ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን»
>
> (2 ቆሮ. 5፡17-20)

እውነተኛ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ይህንን በእምነት ይቀበላል። በመረጃ የበለጸገ እውነት ስለሆነም በሕይወቱ ይለማመደዋል። ይህ ገሐድ ነውና!

ምናልባት ይህን መቀበል ለአንተ ሊከብድህ ይችላል። ይህን ከልጅነትህ እንድትቀበል በመደረግህ ብቻ ሳይሆን፥ የ «ክርስትና» አመዛኙ ክፍል የዚህ የ «አዲስ ፍጥረት» ምስክር መሆን አልቻለም። ለዚህ ምክንያቱ ግልጽ ነው፡- በቤተ ክርስቲያን አባልነት ከተመዘገቡት ብዙዎቹ ከኃጢአታቸው ተጸጽተው የእግዚአብሔርን ስጦታ

በእምነት አልተቀበሉም። ስለዚህም በይቅርታው የሚገኘውን ደኅንነትና በዚያ ውስጥ ያለውን ምስክርነት ያጣሉ። ይቅርታና ራስን ለእግዚአብሔር መንገድ ማስገዛት የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው።

በማጠቃለያ ለአንተ ያለኝን እውነተኛ ፍቅርና የአክብሮት ሰላምታ ላስተላልፍልህ እፈልጋለሁ።

ያንተው፥

ቴዎፍሎስ

# ቁጥር 4

ውድ ዐብደላ፥

ደብዳቤህን ምን ያህል እንዳደነቅሁት ልነግርህ አልችልም። የተለያየ የሃይማኖት መረዳት ቢኖረንም ቅሉ ግንኙነታችን ሁልጊዜም መከባበርና ግልጽነት ያለው እንደሆነ ባመገመቴ የተሳሳትሁ አይመስለኝም። ዘላለማዊ ጉዳዮችን የማስተዋል አስፈላጊነት የምታውቅ ሰው ትመስላለህ።

እኔ፥ በስሜት የበለጸገ ሕይወት ጥሩ መሆኑን ባምንም፥ መንፈሳዊ ውይይታችን ግን መገዛት ያለበት ለስሜት ሳይሆን፥ ለሐቀኛ እውነት ነው። በእርግጥ ይህ ቅር ሊያሰኝ ይችል ይሆናል። ስለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ «እውነትን በፍቅር» እንድንናገር የሚያስተምረን (ኤፌ. 4፡15)። አንድ ሰው ሲናገር፥ እውነት ያለ ፍቅር ጭካኔ የተሞላበት ነገር ሲሆን፥ ፍቅር ያለ እውነት ደግሞ ስሜታዊነት ነው፥ ያለው ትክክል ነው። እውነትና ፍቅር አንድ ላይ የሚሄዱ ነገሮች ናቸው።

ወደ ደብዳቤህ ስመለስ፥ ብርቱውንና፥ ለታማኝ የሃይማኖት ተማሪ ደግሞ ግልጽና አሳማኝ የሆነው፥ የተፈጸመ ትንቢትን፥ የዓይን ምስክሮች ዘገባና የታሪክ መረጃን ተመልክተሃል። በመጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ያለን የመተማመን መልሕቅ ይህ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በሚገለበጥበት ጊዜ የተከሰቱ በጣም መጠነኛ የሆኑ ስሕተቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ብንቀበልም፥ ይህ የእግዚአብሔርን ቃል መልእክትም ሆነ ይዘት ሊለውጥ እንደማይችል በጣም እርግጠኞች ነን! እስከ 3000 ዓመታት ያህል በእጅ እየተገለበጡ የኖሩት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በውስጣቸው በሺህ የሚቆጠሩ ተጨማሪ ስሕተቶች አለመያዛቸው እራሱ ግልጽ የሆነ ተአምር ነው የሚያሰኝ ነው። ክርስቲያን የሆኑና ያልሆኑ በርካታ የሊቃውንት ቡድኖች እያንዳንዱን መጽሐፍ በጥብቅ መርምረው አጥንተዋል። ይህም አልፎ አልፎ የሚታየውን ስሕተት፥ ለመለየትና ወደ ኋላ ተመልሰው መቼ ጣልቃ እንደገባ ለመጠቆም ረድቷል። ከዚህም የተነሣ ወደ መጀመሪያውና ወደ ፍጹም ራእይ በጣም የቀረበ ቅጂ በእጃችን እንዳለን እርግጠኞች እንሆናለን።

በዚህ በኩል ክርስቲያኖች የሚያሳዩትን ግልጽነት አንዳንድ የሙስሊም ሊቃውንት አግባብ ባልሆነ መንገድ ሲያቀርቡ ስናይ በእጅጉ ይሰማናል፤ ብሎም ያስቆጣናል። መጽሐፍ ቅዱስ ብለን የምንጠራውን መለኮታዊ ራእይ ዋጋ ለማሳጣት፥ ዘመናዊነት በሚከጅላቸው (የሥነ-መለኮት ምሁሮቻቸው የመላምቶችና መሠረት የለሽ መግለጫዎችን ያቀርባሉ። በሌላ በኩል፥ ምንም ቁርዓን የመጣው ከመጽሐፍ ቅዱስ በኋላ ቢሆንም ተመሳሳይ፥ እንዲያውም የባሱ ውስብስብ ችግሮች እንዳሉት ለመቀበል አይፈልጉም። መቼም ይህ ዐረፍተ ነገር አዳጋች እንደሚሆንብህ ይገባኛል። ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ከሚሰነዘሩብን ከበርካታ እስላማዊ መግለጫዎች እኛን

ቅር ከሚያሰኙት በላይ እንደማይሆንብህ እርግጠኛ ነኝ። እስቲ ለማለት ያሰብኩትን ላብራራ እውነቱን በፍቅር ለማቅረብ ከልቤ እጥራለሁ።

በደብዳቤህ በሁሉም ሙስሊሞች ዘንድ ጠቅላላ ተቀባይነት ያለውን አመለካከት አንጸባርቀሃል። ይህም አመለካከት አሁን ያለው ቁርዓን መጀመሪያ ከተገለጸው ራእይ ጋር አንድ ዓይነት እንደሆነ የሚገልጽ ነው። እያንዳንዱ የእስልምና ሊቅ እንደሚረዳው፥ ከመጀመሪያዎቹ ካሊፎች ዘመን ጀምረው ያሉት የእስልምና ባህሎች ግን ይህንን አሳብ አይቀበሉም።

ይህንን ከመመልከታችን በፊት፥ እስቲ ወደ ደብዳቤህ ተመልሼ ላጣቅስ። ቁርዓን የእግዚአብሔር ራእይ እንደሆነ የሚሳምኑህን ሦስት ምክንያቶች ገልጸሀል። እኔ እንደማስበው፥ ይህን ያልኸው መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተላከ ለመሆኑ በማስረጃነት ለሰጠሁህ ምላሽ እንዲሆን መሆኑ ነው። በሥነ-ጽሑፋዊ ጥራቱ ስለተደነቀው የግጥም ሥርዓቱ፥ ስለ ቁርዓን ይዘት፥ ብዙ ሙስሊሞች የቁርዓንን ሙሉ ክፍሎች በልባቸው እንደሚሸመድዱ ቸውና ቁርዓንም በፍጹም ሳይለወጥ በሙሉነቱ ተጠብቆ እንዳለ ጠቅሰህልኛል። ትንሽ መሠረታዊ የቁርዓን ዕውቀት ያለው ሰው እንኳ፥ ቢያንስ የቁርዓንን የመካ ሱራዎች ውበት ለማድነቅ ችግር አይገጥመውም። ዳሩ ግን መረዳት ያለብን በጣም ማለፊያ የሆነው የሰው የሥራ ውጤት እንኳ ቢሆን መለኮታዊ ተደርጎ መወሰድ እንደሌለበት ነው። የመለኮታዊ ነገር መለኪያው ሰው ከሚሠራው በላይ ልቆ መገኘቱ ሲሆን ነው። ይኸውም እንደተፈጸመ ትንቢት ዓይነት ነገር ነው።

የቁርዓንን ይዘት በተመለከተ፥ እኛ ክርስቲያኖች መቼም ከወንጌል ወይም ከአዲስ ኪዳን ጋር እንደምናወዳድረው የታወቀ ነው። በሙሉ ታማኝነትና ሐቀኝነት የቱን ያህል ጥረት ብናደርግም እንኳ ከብዙ ምክንያቶች የተነሣ የማያሻማ ምርጫችንን ለወንጌሉ ለማድረግ እንገደዳለን። ዳሩ ግን እነርሱን እዚህ ላይ ማብራራቱ ከዚህ ደብዳቤ ዓቅም በላይ ይሆናል።

ቁርዓንን በቃል የመውጣቱ ጉዳይ ደግሞ ሌላ ነው። ምናልባት እዚህ ላይ ከፍተኛ ሚና የሚጫወተው ብሩህ አእምሮ፥ ትጋትና የያዘውን የማይለቅ ልዩ አእምሮ ሊሆን ይችላል። ይህ ዕውቀት ሳይማሩ እንዲሁ የተገኘ ቢሆን ኖሮ ተአምራዊ በሆነ ነበር። ያም ቢሆን እንኳ የስውር ኃይል/ሉች/ ጣልቃ ገብነት ሊሆን እንደሚችል አንዘንጋ።

አሁን ግን ወደ መጀመሪያው ነጥባችን እንመለስና፥ ቁርዓን ሙሉ ለሙሉ ተጠብቆ እንዳለ የሚናገረውን መግለጫ እንመልከት። በዚህ ደብዳቤ ውስጥ አባባሎቼን ሁሉ ማጠናከር የማይቻል ነገር ነው። አንተ ከጠየቅኸኝ ግን በደስታ ይህንን አደርጋለሁ። ይህም ፍሬ ወደሌለው ክርክር እንደማይወስደን ተስፋ አደርጋለሁ። በመሐመድ የሕይወት ዘመን ውስጥ «ሰባት ዓይነቶች» የተባሉት የቁርዓን የቃል ጥናቶች በጥቅም ላይ እንደነበሩ፥ በእስልምና ባህሎች የተደገፈ ነው። መሐመድ ራሱ፥

«ይህ ቁርዓን በሰባት ዓይነቶች የተገለጸ ስለሆነ፥ ከሁሉ ቀላል በሆነው መንገድ ድገሙት» ብሏል (ሚሽካት 3፥ ገጽ 702፤ የአትባሪ ታፍሲርና የአል - በለጽ ትርጓሜ)።

በተጨማሪም የዑስማን መጽሐፍ የሆነው ቁርዓን የቀደሙት መጻሕፍት ቅንብር እንደሆነ መረዳት አለብን። በአቡ በከርና ዑመር አማካሪነት ዛይድ ቢ ታቢት ካሰባሰበው ከሁሉም በላይ ታዋቂ ከሆነው ቁርዓን በተጨማሪ፥ ሌሎችም በርካታ የቁርዓን መጻሕፍት ይገኛሉ። እነዚህም መጻሕፍት የተዘጋጁት እንደ ዐብደላ ቢ.ማሱድ፥ አባይ ቢ.ቃብ አባ ሙሳ በመሳሰሉ ከዛይድ የተሻለ ድርጅት በነበራቸው ሰዎች ነው። ምንም እንኳ ቁርዓን በዑስማን ከተቀነባበረና ከተዘጋጀ በኋላ የእነርሱ መጻሕፍት ቢታገዱና በኋላም እንዲወድሙ ቢደረጉም፥ ብዙዎቹ ጽሑፎቻቸው በሥነ-መለኮት ሰነዶች መካከል ስለተገኘ ከዑስማኑ ጽሑፍ ጋር ሊነጻጸሩ ይችላሉ። ከበርካታ ጥቃቅን ልዩነቶች በተጨማሪ፥ አንዳንዶቹ ከሌሎች የበለጡ «ሱራዎችን» ወይም «ኢያዎችን» ይዘው ይገኛሉ። በዛይድ የተዘጋጀውና በሐፍሳ እጅ የነበረው ቅጂ ማርዋን እብን-አል-ሃካም በተባለው ገዥና መዲና መቃጠሉ እንኳ ለእኛ ትርጉም ይሰጠናል። (እብን-አቢ-ዳውድ ገጽ 24፥25፥ እና እብን ዓሳኪር ቅጂ 445)። የመጻሕፍቱ መለወጥ፥ መጨመርና መቀነስ በግልጽ የሚታወቅ ነገር ነው።

ይህ ሁሉ እንግዲህ አንድን ገናና ሃይማኖት በቀላሉ ከመቀበል እንድንቆጠብ ያስተምረናል። ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ መሃይማን ሰዎች በታማኝነት እንዲከተሉት ተደርጎ በተማሩ ሰዎች የተቀነባበረ በመሆኑ ነው። ይልቁንም ለሚያምን ልብ ተመራማሪ አእምሮ ልንቸረው ይገባናል። ይህ ግን በእግዚአብሔር ላይ ሳይሆን እኔንም ጨምሮ በሰው ሁሉ ላይ ሊደረግ ይገባዋል።

አንተም እንደ እኔው በእስልምናና በመጽሐፍ ቅዱስ ራእዮች መካከል ያሉት ልዩነቶች ውስብስብና በጣም መሠረታዊ እንደሆኑ ሳትረዳ አልቀረህም። ይህም መረዳት እርስ በእርስ መደማመጥና እምነትን የእግዚአብሔር ማኅተም ባረፈበት ጉዳይ ላይ ማድረግ የማይቀር ጉዳይ ያደርገዋል። ስለሆነም ታማኝነታችን በመረጃዎች በበለጸገው፥ ፍቅርና ብርታት ሊደገፍ ይገባዋል።

ያንተው፥

ቴዎፍሎስ

## ቁጥር 5

ውድ ዐብደላ

ስለ ፈጣኑ ምላሽህና ደብዳቤህ ስለተጻፈበት መንፈስ በጣም አመሰግንሃለሁ። ውይይታችንም ውስብስብ እያለ የመጣ ይመስላል።

ስለሆነም ያለምንም መዘግየት የደብዳቤህ ምላሽ ዋና ነጥብ ወደሆነው «የበርናባስ ወንጌል» ልምጣ። በእርግጥ ስለዚህ ጉዳይ ሰምቼአለሁ። እንዲያውም ብዙ ክፍሉን አንብቤዋለሁ። አንተም ስትጽፍ፥ «ይህ የመጀመሪያው ወንጌል ይመስለኛል ከቀድሞው ክርስቲያናዊ አመለካከት ጋር ስላልተስማማም፤ የቤተክርስቲያን መሪዎች አግልለውታል። እርሱም አሁን በአዲስ ኪዳን በሚገኘው ወንጌል ተተክቷል፤ ይሁን እንጂ ይህ ወደ ጳውሎስ የሥነ-መለኮት ትምህርት በእጅጉ ያጋደለ ነው። ይኸውም የኢየሱስ መለኮታዊነትና ልጅነት፥ ሥላሴ፥ የስቅለቱና የስርየቱ ትምህርት ነው» ብለሃል።

መቼም እነዚህን ሁሉ አደገኛ ነጥቦች በአንድ ጊዜ ለመጋፈጥ ባለመቃጣቴ ይቅር ትለኛለህ። አሊያም ይህ ደብዳቤ በጥቅል ፖስታ መላክ አለበት ማለት ነው። ይሁንና እስኪ ስለ «በርናባስ ወንጌል» ጥልቅ እይታ እናድርግ።

እስከአሁን ድረስ ታሪካዊ የልብ-ወለድ መጽሐፍ ጽፈህ የምታውቅ አይመስለኝም። ጽፈህ ቢሆን ኖሮና መጽሐፍህም ታሪካዊ እንዲሆን ከታለመ፥ በሺህ የሚቆጠሩ ነገሮችን በጥልቅነትና በዝርዝር ማወቅ እንደነበረብህ ትገነዘብ ነበር። በአካባቢው ስላለው መልክዐ-ምድር፥ ባህል፥ የአሠራር ዘዴዎች፥ የኑሮ ሁኔታዎች፥ አለባበስ ወዘተ. ጠንቅቀህ ለማወቅ ትገደዳለህ። በጊዜው የታወቀውን ነገር ከግምት ታስገባለህ፤ እንዲሁም በኋላ የተደረሰበትንና በፈጠራ የተሠራውንም ታስበዋለህ። በተለይም አንድ ሰው ጽሑፉን ልክ በዚያው የጊዜ ገደብ እንደተጻፈ አስመስሎ ለማቅረብ ቢፈልግ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ይሆንበታል። በጣም ከፍተኛ ደረጃ ካለው ምርምር ጋር መፋጠጥ ሊኖርበት ነው። እንደ እውነተኛ ነገር ሰዎች ይቀበሉታል ማለት ቀብደ-ተስፋ ነው የሚሆነው። በቅርቡ የተገኙት «የሂትለር ማስታወሻዎች» (ዲያሪስ ኦፍ ሂትለር) አሳቤን ያጠናክሩታል። እኚህ እንግዲህ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ናቸው።

የባርናባስ ወንጌል የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር ነው በሚባለው በበርናባስ እንደተጻፈ ያስመስላል። በመጀመሪያ ደረጃ ልብ ማለት ያለብን እርሱ ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት አንዱ እንዳልነበር ነው። በርናባስ በመጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው ከኢየሱስ ሞት በኋላ ነው (የሐዋ. 4፡36፥37)።

ቀጥሎ መጽሐፉን እስቲ እንመልከት። አሁን ካለው አንድ የጣልያንኛ ቅጂ በተጨማሪ፥ ሌላ የምናውቀው በእስፓንኛ እንደነበረና አሁን ግን እንደጠፋ ብቻ ነው። ስለ በርናባስ ወንጌል አመጣጥ የምናውቀው ቢኖር፥ በ 18ኛ ክፍለ ዘመን በጆርጅ

ሰየል ወደ እንግሊዝኛ ከተተረጎመው ቁርዓን መቅድም ላይ ከተወሰደው ማስታወሻ ብቻ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ ለዚህ ታሪክ ትኩረት መስጠቱ ጠቃሚ አይደለም። ነገር ግን ወደ በርናባስ ወንጌል ይዘት መመልከቱ ግን አስፈላጊ ነው።

ከሁሉ አስቀድሞ ትኩረታችንን የሚስበው ጉዳይ ደራሲው ስለ ፍልስጤኤም መልከዐ-ምድር በጣም ትንሽ ወይም በሥፍራው የነበረ ሰው የሚኖረው ዓይነት ዕውቀት የሌለው መሆኑ ነው። ከኢየሱስ ጋር በዚህች ትንሽ አገር ከወጣና ከወረደ በኋላ ይህ ሊኖረው በተገባ ነበር። ከገሊላ ሐይቅ ሰሜናዊ ወገን የምትገኘውን የቅፍርናሆም መንደር ውሰድ። የበርናባስ ወንጌል ጸሐፊ ወደዚያ እንደወጣ ይተርካል (ምዕራፍ 21)። ይህ ሊሆን ግን አይችልም። ምክንያቱም መንደሯ ከባሕር ወለል ከ200 ሜትር በታች ዝቅ ያለች፥ ከምድር ገጽ ሁሉ ዝቅተኛዋ ከተማ ናት። ወደ እርሷ ለመሄድ ወደ ላይ መውጣት ጨርሶ አይቻልም። በሚቀጥለው ምዕራፍ ኢየሱስ በጀልባ ወደ ናዝሬት ስለ መሄዱ ይነግረናል! ይህች ከተማ ከባሕር ወለል 500ሜ. በሚገመት ክልል በላይ የምትገኝ ስትሆን፥ በተራራዎች የተከበበች ነች። እንግዲህ አንድ ሰው ጀልባዉቱን ወደ ተራራው መሸከም አለበት ማለት ነው። እንዲያውም ምዕራፍ 151 ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በጀልባ እንደገባ ይናገራል። ይሁን እንጂ ካርታውን መመልከት ይህን አሳብ ፉርሽ ያደርገዋል።

ምናልባት ኢየሱስ በቤተልሔም በተወለደ ጊዜ ወደ እርሱ ስለመጡት ስለ «ሦስቱ ምሥራቃውያን አዋቂዎች» ታሪክ ሰምተህ ይሆናል። የባርናባስ ወንጌል ሰዎቹ ሦስት እንደነበሩ ይገልጻል። በእርግጥ ቁጥራቸውን የሚያውቅ ማንም የለም። እጅግ ዘግይቶ የመጣው ባህል ለኢየሱስ የቀረቡለት ሦስቱ ስጦታዎች (ወርቅ፥ ዕጣንና ከርቤ) በሦስቱ ሰዎች የቀረቡ መሆን አለባቸው ይላል። በተመሳሳይ መንገድ የመካከለኛው ዘመን ባህልና የባርናባስ ወንጌል በዒደን ገነት ሔዋን ስለበላችው «አፕል» ይናገራሉ (ምዕራፍ 40 እና 41) የዚህ መረጃ ብቸኛ ምንጭ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ግን ፍሬ ከማለት በቀር፥ «አፕል» መሆኑን አይገልጽም።

ምዕራፍ ሦስት የኢየሱስ ልደት ምጥ-የለሽ እንደነበረ ይነግረናል፤ ይህም ባህል ከቶማስ አኩይናስ (እ.ኤ.አ. በ1274 ዓ.ም. የሞተ) በኋላ የተገመተ ነው። ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ ያቆጠቆጠውን «ድንግል» የሚለውን ለማርያም የተሰጣትን ማዕረግ በባርናባስ ወንጌልም ውስጥ እንግዳ ነገር ነው። በእርግጥ የባርናባስ ወንጌል ደራሲ ከቤተክርስቲያን ባህሎች ጋር በእጅጉ ተዋውቆ እንደነበር እንመለከታለን። በቅዱሳን መጻሕፍት ስለሌለውና በቅድመ-መካከለኛ ዘመንም ስለተከሰተውም፥ ስለ አራት ሊቃነ መላእክት በውስጡ ተጽፎ እናነባለን። ከዚያም ኢየሱስ «ዓርባ ቀናት» ከደቀመዛሙርቱ ጋር እንዳሳለፈ (ምዕ. 91 እና 92) እናነባለን። ክፍሉ በግልጽ እንደሚያሳየው ይህ ከፋሲካ በፊት ያሉትን ዓርባ የጾም ቀናት የሚያመለክት ነው። ይህ ወቅት በብዙ አብያተክርስቲያናት ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥቃይና ሞት ላይ አጥልቀው የሚያስቡበት ጊዜ ሲሆን፥ ማብቂያውም

የሶ ኦስት ቀን የሆነ ዕለተ-ዓርብ ነው። ይህ ባህል የተጀመረው ከ4ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ በመሆኑ፥ ኢየሱስ በሕይወት በነበረ ጊዜ ይህን ነገር መከናወኑ የማይመስል ነው።

ገንዘብን በተመለከተ (ምዕ. 54)፥ በ60 «ሚኑቲ» የሚመነዘር ዲናር ተጠቅሷል። በኢየሱስ ጊዜ የሚታወቅ ምንም «ሚኑቲ» አልነበረም። «ሚኑቲ» በነጋንኝ ገንዘብ ሆኖ ለመለዋወጫነት ያገለገለው እ.ኤ.አ. በ685 ዓ.ም. በቃሊፋ ዐብዱል ማሊክ አገዛዝ ሥር ነው።

ሌላው ችግር ደግሞ ወታደሮቹን ልኮ «የእንጨት በርሜሎች እንደገና ወይን ከተሞላታቸው በፊት ሲታጠቡ እንደሚንከባለሉት፥ ከመቅደስ እያንከባለለ አስወጣቸው» በሚለው ታሪክ በምዕ. 152 ውስጥ የሚገኘው ነው። እውነተኛው ጸሐፊው የእንጨት በርሜሎች ጋል በሚባል ሥፍራ በጣም ዘግይተው እንደተሠሩና በኦየሱስ ጊዜ ወይን በአቁማዳ ይቀመጥ እንደነበር አለመረዳቱ ግልጽ ነው። ሌላው ትኩረትን የሚስበው ነገር፥ ኢየሱስ የተወለደው ጲላጦስ አገረ-ገዥ በነበረ ጊዜ እንደሆነ የቀረበው ዘገባ ነው። በመሠረቱ የጲላጦስ አገዛዝ ዘመን የጀመረው እ.ኤ.አ. በ26ና 27 ዓ.ም. መካከል ነው።

ምናልባት የባርናባስ ወንጌል የቅርብ ዘመን ክስተት ለመሆኑ ከሁሉም በላይ ገላጭ የሆነው መረጃ የሚገኘው በሁለት ሐቆች ላይ ነው። በመጀመሪያ፥ ደራሲው በተለይ እርሱ በሕይወት በነበረበት ወቅትና ከዚያም በኋላ ለአጭር ጊዜ ተወዳጅ ከነበሩት ከኦጣልያዊው ገጣሚ ከዳንቴ (1265-1321) ግጥሞች ውስጥ በተደጋጋሚ መጥቀሱ ነው ። ሁለተኛ፥ የመጽሐፍ ቅዱሱ «ኢዩቤልዩ» በየአምሳኛው ዓመት እንደሚከበር እናውቃለን (ዘሌዋውያን 25)። የቤተክርስቲያን ባህል ይህንን በክፍለ ዘመኑ መጀመሪያውና በመካከለኛ አድርጎት ነበር። ከዚህ የተለየ ነገር የተፈጸመው አንዴ ብቻ ነበረ። ይኸውም አምሳኛው ዓመት በፖፕ ቦኒፌስ 8ኛ እ.ኤ.አ. በ 1300 ዓ.ም. ወደ መቶ ዓመታት መለወጡ ነው። ታዲያ የባርናባስ ወንጌል (ምዕ. 82) የኢዮቤልዩ ዓመት «አሁን በየመቶ ዓመት ይመጣል» ቢል፥ ሊያስገርመን ይችላል'ነ

ምንም እንኳ በርካታ እስላማዊ አስተሳሰቦች አልፎ አልፎ የተጠማጠሙበት ቢሆንም፥ የባርናባስ ወንጌል መሠረታዊ የእስልምና እምነቶችን እንደሚቃረን መረዳት ያለብን ይመስለኛል። በምዕራፍ 97ና በሌሎችም ሥፍራዎች መሐመድ መሢሕ እንደሆነ ተገልጿል። ኢየሱስም ክርስቶስ ተብሏል። በእርግጥ ክርስቶስ የሚለው የግሪክ ቃል መሢሕ የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ትርጉም ነው።

የባርናባስ ወንጌል የተጭበረበረ ቅጂ መሆን እንዳለበትና ዕድሜውም የተገመተው ደራሲ ከኖረበት ዘመን በኋላ ከ1300-1350 ዓመታት የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደሚገባ ከእኔ ጋር ትስማማለህ። እዚህ ላይ መነሣት የሚችለው ተገቢ ጥያቄ የተጻፈው ለምን ነበር? የሚል ነው። የተጻፈበት ዓላማ መኖር አለበት። እዚህ ላይ እንኳ መልሱ በተዘዋዋሪ መንገድ «በወንጌል» ተሰጥቶአል። እስልምናን በማስፋፋት የሚያገለግል

መሣሪያ ሆኖ ቀርቧል። ነገሩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ዘወር ተደርጎ የተወሰደ ለእስልምና ጥቅም ሲባል ነው። ይኸውም፡- ኢየሱስ ሳይሰቀል በመላእክት በመወሰዱ፥ ይሁዳ በቦታው ተሰቀለ (ምዕ. 222) የሚል ነው። በአብርሃም ወደ መሠዊያው የቀረበው እስማኤል (ምዕ. 44) እንጂ፥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ይስሐቅ አይደለም (ዘፍ. 22)። እግዚአብሔር የሚናገረው የአብርሃም፥ የእስማኤልና የይስሐቅ አምላክ እንደሆነ እንጂ፥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ አይደለም።

በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ሳይሆን፥ ቁርዓንንም ጭምር የሚቃወመው ታውራት በእስማኤላዊ እንደተጻፈ (ምዕ. 192) የሚገልጸውን ክፍል ማንበብ በይበልጥ ያስደንቀናል። መሐመድ በተደጋጋሚ መጠቀሱ እና (ምዕ. 44፥ 45፥ 97፥ 112 ና 163)፥ አዳምም በደማቅ ጽሕፈት ሰማይ ላይ ማየቱ በመጠኑ ያስገርማል! (ካሊማን ምዕ. 39)።

ሙስሊሞች ከላይ የተጠቀሱትን ዓይነት ግንኙቶች እያወቁ እንኳ፥ እንዲህ ዓይነቱን የተጨበረበረ በቅጂ በመጠቀም ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለመቀስቀስ ማዋላቸው ለክርስቲያኖች እንግዳ ነገር መሆኑ የሚያስገርምህ አይሆንም። ለመሆኑ እንዲህ ያለ መናኛ ሰበብ አስፈላጊ ነውን?

በማጠቃለያው፥ ከተፈጥሮዬ ውጭ ጨካኝ ሆኜ ስለቀረብሁህ፥ ይልቁንም በቀጥታ አሳቤን ስላስተላለፍሁልህና ምናልባትም ተቃዋሚ ሆኜ ስለተገኘሁ፥ ይቅርታ ለመጠየቅ እፈልጋለሁ። በማንኛውም መንገድ አንተን ለመጉዳት እንደማልፈልግ አሳምረህ ታውቃለህ። ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን እውነት የሚፈታተን ሐሰተኛ ነገር ሲያጋጥም ቁጣዬን ማፈኑ ይሳነኛል። ይህንንም ስል እባክህ አንተ ሐሰተኛ ነህ ማለቴ እንዳልሆነ ተረዳልኝ። ለስውር ቅጥፈት እንደተጋለጥህ እርግጠኛ ነኝ። ዳሩ ግን ምንጩን እያወቁ ይህንን ወንጌል ለግል ጥቅም ሲባልና ከእውነተኛው የኢየሱስ ትምህርትና እውነተኛ ወንጌልን ለመቃወም መሣሪያ አድርገው የሚያቀርቡትን ሰዎች አጥብቄ እቃወማለሁ።

ለቤተሰቦችህም ደግሞ የከበረ ሰላምታዬን አድርስልኝ!

ያንተው

ቴዎፍሎስ

# ቁጥር 6

ውድ ዐብደላ፥

ስላለፈው ደብዳቤህ፥ በተለይም የእምነታችንን ዋነኛ ፍሬ ነገሮች ወደ ሆነው እንድንመለስ ስለሰጠኸኝ አስተያየት በጣም አመሰግንሃለሁ። በእርግጥ የእምነታችን መሠረቶች የሆኑትን መጻሕፍት ለተወሰነ ጊዜ በማስተዋል ከተመለከትሁ በኋላ፥ ይዘታቸውንም መገምገሙ በጣም መልካም ነው።

አሁን ዕለት በዕለት በሕይወታችን ላይ ተጽዕኖ ስለሚያደርሰውና ከዚህም የተነሣ በጣም አንገብጋቢ ስለሆነው ጉዳይ፥ ስለ ኃጢአት፥ እንድናነሣ አሳብ ላቅርብ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ፥ ባለማቋረጥ ውስብስብ ስለሆኑት ጉዳዮች የምንነጋገር ይመስላል። ኃጢአት የሚለው ቃል በጣም ቀላል ቃል ነው። ጸሩ ግን ለዚህ ቃል የተለያዩ ይዘቶች መስጠቱ የሚዘወተር ነገር ነው። እስቲ ለዚህ ቃል እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰጠውን ትርጉም ለመግለጽ ልሞክር።

እስቲ ከመጀመሪያ ልጀምር፡- እስቲ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በመጀመሪያ በተጻፉበት በዕብራይስጥና በፊክ ቋንቋዎች ከዚህ ቃል ጋር የተያያዘውን ትርጉም እንመልከት። በዚያ የተጠቀሰው ቃል ምልክት ወይም ዓላማ ስለጠፋበት ሰው ይገልጻል። ጦረኛ ሰው ቀስትና ፍላጻ በመውሰድ ወዳለመበት ዓላማ ያነጣጥራል። ሆኖም ዒላማውን ይስታል! ስለዚህም ዕቅዱ ከግብ ሊደርስ አልቻለም። የተሳተው በአንድ ኪሎ ሜትር ወይም በአንድ ሚሊ ሜትር ርቀት ቢሆን ለውጥ የለውም። ከዓላማው ላይ አነጣጥሮ ለማሳረፍ የነበረው መሻት ቢሆን ምንም አልፈየደም። በመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት የመጀመሪያ ቋንቋ ውስጥ «ኃጢአት» ን ለማመልከት የቀረቡት ሌሎች ቃላት፡- ከተወሰነው መንገድ መውጣት፥ መብት ባለው ባለሥልጣን ላይ ማመፅ፥ ሕግን መተላለፍ፥ ቃል ኪዳንን ማፍረስ፥ ታማኝ ያለመሆን፥ ከዳተኝነት ከንቱነት ናቸው። እነኚህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር የተዛመዱ ናቸው። ከሥር መሠረቱ ያለው ግን «ከእግዚአብሔር ይልቅ ለእራስ መሠረታዊና እርግጠኛ ቅድሚያ መስጠቱ» ላይ ነው። (ኤ. ኤች. ስትሮንግ)።

እግዚአብሔር ስለፈጠረንና አምላካችንም ስለሆነ፥ ከእያንዳንዳችን ሙሉ ተገዢነት መፈለጉ መብቱ እንደሆነ እንደምንስማማ እርግጠኛ ነኝ። ለእኛ ያለውን ፈቃድና ዓላማ እንረዳ ዘንድ፥ በቃሉ ውስጥ ገለጸልን። ይህም በሚከተሉት ዓይነት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ጎልቶ ይንጸባረቃል፡-

> «እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኩራት መርጦአችኋልና»
>
> (2 ተሰ. 2፡13 )
>
> «ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ» (ኤፌ. 4፡24)። «ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም

መቀደሳችሁ ነውና»

(1 ተሰ. 4:3)

ቅድስና የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙም ለእግዚአብሔር ለራ መለየት ማለት ነው። ይህ በእርግጥ የራስን ክብር ከሚፈለገው ከተፈጥሮአችንና ግ ዊ ፍላጎታችን ጋር ግብግብ መፍጠሩ የማይቀር ነው። እግዚአብሔርን ለማክበ ና ለማስደሰት በጣርን ቁጥር፥ የእኔነት ጥያቄ እያየለ መምጣቱ የታወቀ ነው። እግዚአብሔርም ይህንን ነገር ያውቀዋል። በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ እንደሚከተለ ው ተገልጿል፡-

«የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና፤ ዳሩ ግን የምወደ ን እርሱን አላደርገውም . . . በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁ፤ ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም»

(ሮሜ 7:15-18)

ማንም መጠነኛ ታማኝነት ያለው ሰው የዚህን ዐረፍተ ነገር እውነትነት መቀበል አለበት። ይሁንና ከልባችን ጓዳ ውስጥ፥ «በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይ ር አውቃለሁ» የሚሉትን ቃላት እንፀየፋቸዋለን። ይህንንም የምናደርገው ትዕቢታች ን ስለሚያኮስስብን ነው። ትዕቢት ደግሞ ከሁሉ የከፋ ኃጢአት ነው። ከእኛ ው በተቃራኒ፥ እግዚአብሔር ስለ ጽድቅ ያለውን አመለካከት አጥብቀን ከመረመ ን ይህንን እንረዳለን።

«ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደ ኛ ይሆናል»

(ያዕ. 2:10)

በሌላ በኩል እኛ፥ ከእግዚአብሔር ሕግጋት ጋር የሚስማሙት ሥራዎ ን ከ51-49 ከሆኑ፥ በእግዚአብሔር ፊት ብቁ እንደሆንን ወደ ማሰብ እናዘነብላለ ። እግዚአብሔር ግን እንዲህ አያስብም።

ዳዊት «ሕያው ሁሉ በፊትህ ጻድቅ አይደለም»

[መዝ. (143):2] ይላል።

«የማይበድልም ሰው የለም»

(1 ነገሥ. 8:46)።

«ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለ »

(1 ዮሐ. 1:8)።

ይህንን የእግዚአብሔርን አቋም መረዳታችንና ለዚህም መረዳት የምንሰጠ ው ምላሽ የዘላለም ዕድላችንን ይወስነዋል። በመጀመሪያ ደረጃ ምላሻችን ሊ ን

የሚችለው ሌላ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ፍርድ መስማማት ነው። ይህም ወደ ይቅርታውና ምሕረቱ የሚወስደውን በር ወለል አድርጎ ይከፍትልናል።

ኃጢአትን ከማንነታችን አኳያ ሳይሆን ከምንሠራው ሥራ አንጻር መመልከቱ አዲስ ነገር አይደለምን? በእግዚአብሔር ዘንድ መኮነናችን ወይም ተቀባይነት ማግኘታችን የሚወሰነው ባደረግነው ወይም ባላደረግነው ነገር አይደለም! ከእርሱ ዘንድ የኃጢአት ይቅርታ አግኝተን በዚያው ይቅርታ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ አለመታረቃችን እንጂ! ስውር የሆነውን ልዩነት ልንገነዘብ ይገባናል። ኃጢአተኞች የሆንነው ኃጢአት ስለምንሠራ ሳይሆን፥ ኃጢአተኞች ስለሆንን ነው ኃጢአት የምንሠራው። ወደድንም ጠላንም በእያንዳንዳችን ውስጥ ወደ ኃጢአት የሚነዳን ሥር የሰደደ ኃይል አለ። ቢሆን እንጂ ኃጢአት መሥራት እንደሚችል መመሪያ መቀበል አላስፈለገውም። ትክክል የሆነውን ነገር ለማድረግ ብዙ ጥረት ሲጠይቅ መዋሸት፥ ሐሜት፥ ቅናት፥ ምኞት፥ ወይም ተግባቢነት ወደማጣትና መለማመዱ ግን ያለችግር ይከናወናል። ይህ ዝንባሌ የሚከሰተው ለምንድነው? ከወላጆቻችንና ከቅድመ-አያቶቻችን የወረስነው መሆኑ ግልጽ ነው። ኃጢአትን ማድረግ ልክ እንደ መልካችንና እንደ ባሕሪያችን ሁሉ የእኛነታችን ክፍል ነው። ስለዚህ በገዛ ፈቃዳችን ኃጢአት ማድረግን ለማቆም አንችልም። ለማቆም ብንችል እንኳ፥ ያለፈው ኃጢአታችንስ?

በቀደመው ደብዳቤ ላይ እንደተገለጸው፥ ሁላችንም ራሳችንን በዚህ ግራ መጋባትና ፈተና ውስጥ እናገኛለን። ስለዚህ «በሃይማኖት ገበያ» ላይ ከቀረቡት መፍትሔዎች መካከል ከእግዚአብሔር የሆነው የቱ እንደሆነ ወደ ብርሃን ለማምጣት ጉዳዩን በጋራ አጥብቆ መመርመር እጅግ አስፈላጊ ነው። ሰው ትክክለኛውን መንገድ እየተከተለ እንዳለ መገመቱ የተለመደ ነገር ነው። ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅና ለኃጢአቱ ማካካሻ ለማድረግ ይሞክራል። ይህ ፍርድ ከተሰጠው በኋላ ወንጀለኛው ሰው በደሉን ለማካካስ «መልካም ሥራ» ለመሥራት ወይም ደግሞ ጥፋትን ላለመድገም ቃል ገብቶ በነፃ ይለቀቃል እንደ ማለት ነው።

እዚህ ላይ ብናቆም መልካም ይመስለኛል። የምታስብበት ከቁጥር የበረከተ ብዙ ነገር አለ። እግዚአብሔር ለዚህ የሚሰጠንን መፍትሔ ለሚቀጥለው ደብዳቤ እናቆየው። ይህን ደብዳቤ ፍጹም አሉታዊ ሆኖ ብታገኘው፥ ትክክል ነህ። ጉዳዩ ከእልባት ሳይደርስ በዚህ መቋጨቱ መንፈስን ሊያሳዝን ይችላል። እግዚአብሔር ግን መልስን ይሰጣል። እስከዚያው፥ አስ-ሳላማለ-ኩም!

ያንተው

ፊዎፍሎስ።

# ቁጥር 7

ውድ ዐብደላ

መቼም ያንተ ደብዳቤ ያልጠበቅሁት ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ለዚሁም አብዝቼ ላመሰግንህ እወዳለሁ። በኃጢአት ርዕስ ነገር ላይ እኔ ከጠበቅሁት በላይ ተመሳሳይነት ያላቸው መሠረቶች አሉን። ምንም እንኳ ከአባባልህ ኃጢአት በእስልምና በኩል የሚሰጠው ትርጉም እንደ ጥፋት፥ እንደምንሠራው ስሕተት፥ ባጠቃላይም «የፍታብሔር ጉዳይ» ሳይሆን እንደ «ወንጀል ጉዳይ» መስሎ ቢታየኝም ተግባራዊ እውነታውን ግን ተገንዝበሃል። የምናከናውነው ጥፋትም ሆነ ቸል የምንለው ትክክለኛ ሥራ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ላይ በደልን መፈጸም ነው። ምክንያቱም ትእዛዙን መተላለፍ ስለሆነ ነው። ይህም ሁልጊዜ ጎጂ ተጽዕኖዎች አሉት። እነዚህም ካልነቁና ካልተመለሱ፥ ወደ ፍርድና ኩነኔ የሚያመራ፥ ከእግዚአብሔር መለየትን ያስከትላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ነጥብ ላይ፥ በግልጽ ሲያስቀምጥ «እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ» (ራእይ 20፡13) ይላል። ይህ የፍርዱ ክፍል ነው፤ ኩነኔውስ ምን ይመስላል?

> «በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ»
> (ራእይ 20፡15)

ይህ የሚሆነው ለምን ያህል ጊዜ ነው? ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡-

> «የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤ አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በእርሳቸው ይለያቸዋል፤ በጎችን በቀኙ፥ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል። ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፡- «እናንተ የአባቴ ብሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ . . . በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፡- «እናንተ እርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከኔ ሂዱ . . . እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ»
> (ማቴ. 25፡31-34፥ 41፥46)

ጻድቁ ማን እንደሆነ እንጠይቅ ይሆናል። ስለ ኃጢአት ከተነጋገርን ዘንዳ፥ ስለ ጽድቅም ልንነጋገር ይገባናል። ምናልባት የቃሉ ፍች ማብራሪቱ ተገቢ ይሆናል። ይህም ቀለል ያለጉዳይ ነው። ጽድቅ ማለት በእግዚአብሔር መለኪያ ተለክቶ ትክክል የሆነን ነገር ማድረግ ማለት ነው። በዚህም የጽድቅ ፍች መሠረት፥ በእግዚአብሔር ፊት ማንም ሰው ጻድቅ እንዳልሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስተምር ባለፈው ደብዳቤዬ ጠቅሻለሁ። ሁላችንም ኃጢአት ስለሠራን፥ ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር ምሕረት ላይ እንደገፋለን። ዳሩ ግን በዚህ ውስጥ ምንም አስማተኝነት የለም። ስለሆነም ምሕረቱን በተመለከተ፥ መነሾውንና ውጤቱን በግልጽ አስታውቆናል።

በመጀመሪያ ደረጃ፥ ሁለት የጽድቅ «ዓይነቶች» እንዳሉ ልናስተውል ይገባናል። አንደኛው የእግዚአብሔርን ሕግ ከመጠበቅና ከመታዘዝ የተገኘ ነው። ይህ የሚሆነው

እንግዲህ ከታዘዝነውና ከጠበቅነው ብቻ ነው። የምንጠብቀውም ደግሞ ዘወትር ነው፤ ይህ ሳይሆን ሲቀር፥ እግዚአብሔር ሌላ ዓይነት ጽድቅ ያመጣልናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ አይሁዶች የሚከተለውን እናነባለን፡-

«በእውቀት አይቅኑ እንጂ፥ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁና። የእግዚአብሔር ጽድቅ ሳያውቁ፥ የራሳቸውን ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ፥ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም»

(ሮሜ 10፡2 ና 3)

ከእግዚአብሔር ከሚመጣ ጽድቅ አንጻር፥ የሰውን የግል ጽድቅ ለይተን እናያለን። ከሁሉም በላይ ይቀናና ሕግን ይጠብቅ ስለነበረው ስለ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደምናነበው፥ ያንን ለእርሱ ረብ የነበረውን ነገር እንደ ጉድፍ እንደቆጠረ ነው።

«ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ፥ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት፥ በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ፥ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ፥ በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን (በሕግ በኩል ጽድቅን ለማግኘት የተሠሩትን ሥራዎች) እንደ ጉድፍ እቆጥራለሁ፤ እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ . . . ከሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ»

(ፊልጵ. 3፡8-11)

ስለዚህ ጉዳይ በመጠኑ ማብራራት ያስፈልገኛል፤ ካልሆነ በትክክል አለመግባባት መከሰቱ አይቀርም። እምነት የጽድቅን ሕይወት ይቃረናልን? አይቃረንም፤ አንዲሁም ደግሞ አይተካውም። ዳሩ ግን ሁለቱም በተለያየ ደረጃ ይሠራሉ። ይህን ከመረዳታቸው በፊት፥ እምነት የሚለውን ቃል ማብራራቱ ከማመንና ምናልባትም እርሱን ከመፍራትም በላይ ነው። ይልቁን እምነት ከእግዚአብሔር ጋር መጣበቅ፥ ማመንና በሁኔታዎች ላይ ያልተደገፈ እንደ አብርሃም ያለ መታመን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አብርሃም ሲናገር እግዚአብሔርን አመነ እንጂ «በእግዚአብሔር አመነ» አይልም።

«ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት»

(ዘፍጥ. 15፡6)

ይህም አብርሃም በራሱ ጥረት ያገኘው ጽድቅ አልነበረም። ከሕይወቱ ትክክለኛ ገጽታ ግልጽ ሆኖ የሚታይ ነው። ይህም የሚያስተምረን እውነተኛ እምነት ትክክለኛ ሥራ መሥራትን እንደሚያስከትልና ከዚህ ውጭ ያለው እምነት ግን ግብዝነት እንደሆነ ነው። አማኞች በእግዚአብሔር ቃል ሲያምኑ ሁለት ነገሮችን ይረዳሉ፡-

1. ትክክለኛ ሥራ በመሥራት ደኅንነት ለማግኘት አንችልም፤ ምክንያቱን አስቀድመን ስሕተት ሠርተናልና። እንዲሁም

2. እርሱን በመተማመን ለሚጠባበቁት ሁሉ እግዚአብሔር ጽድቁን ያለብሳቸዋል።

እምነት ኃጢአት በንስሓ መመለስንና የእግዚአብሔርን ስጦታ በእምነት መቀበልን ያካትታል። ይቅርታንም ጨምሮ እግዚአብሔር የሚናገረውን ነገር ሁሉ እንደሚያደርግ እናምናለን። ይህ ማለት ግን ኃጢአትን በመሥራት እንድንቀጥል ፈቃድ እንደማይሰጠን በግልጽ ሊቀመጥ ይገባዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን በግልጽ ያብራራልናል። እነዚህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላቶች ካብራራን ዘንዳ፥ የዚህን ጽድቅ ምንጭ በመጠኑ ጠለቅ አድርገን መመርመር አለብን። ምንጩ እግዚአብሔር ሲሆን የማግኛ መንገዱም በኢየሱስ ማመን ነው። በዚህ ነጥብ ላይ ፍጹም አቋም እንዳለን እንደሚገባህ ተስፋ አደርጋለሁ። ምክንያቱም ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ እምነት ስለሆነ በእርሱ ለመተማመናችን ምክንያቶች ለማቅረብ እንችላለን። ኢየሱስ እንደተናገረው ፍርድን ሁሉ (ዮሐ. 5፡22) እግዚአብሔር አብ ለእርሱ ሰጥቶታል። ይቅርታን ሊሰጥ የሚችል ብቸኛው ዳኛ እርሱ ነው። ዳኑ ግን ለእኛ የተደረገልን ከይቅርታም በላይ ነው፡-

> «በደላቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና»
> (ኤር. 31፡34)

እግዚአብሔር ሊምረንና ይቅር ሊለን እራሱን ዝቅ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፥ ኃጢአታችንንም ፈጽሞ ላያስብና ሊረሳ ቃል ይገባልናል። ምንም ኃጢአት ሠርተን እንደማናውቅ ሊያደርገን ይፈልጋል! ንጹሓን ያደርገናል። እኛም «በሕይወት መጽሐፍ» ውስጥ ተመዝግበናል (ዳን. 12፡1፤ ፊልጵ. 4፡3፤ ራእ. 20፡12፥15፤ 21፡27)። ይህም ወደ ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ክብር መግባታችንን የሚወስን መመዘኛ ነው። በአጭሩ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን፤ ከእርሱም ጋር ታርቀናል።

> «ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን፥ የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው»
> (2ኛ ቆሮ. 5፡18)

ይህ እንግዲህ እግዚአብሔር ለእኛ የሚሰጠን ጽድቅ ነው። እርሱም ኩነኔን ለማስወገድ ሁለንተናዊ ብቃት ያለው ነው።

አሁን እንግዲህ እኛ ክርስቲያኖች ለምን እጅጉን አብዝተን በኢየሱስ ላይ እንደምንደገፍ ትረዳለህ። ወደ ዘላለሙ መንግሥት ለመግባት የእግዚአብሔር መንገድ የሆነው እርሱ ስለሆነ ነው። እራሱም

> «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፥ በኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ብሏል
> (ዮሐ. 14፡6)

ይቅርታን፥ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅንና፥ ጽድቅን ተመልክተናል። ይህን የደኅንነት መንገድ ብለን እንጠራዋለን። እንዲሁም ከማይቀረው የኃጢአት ውጤት መዳኛ ብለን ልንጠራው እንችላለን። ለዚህ ነው ኢየሱስ አሁን በምንጠራው ስም የተሰየመው። ኢየሱስ ወደ አማርኛ ሲተረጎም «አዳኝ» ማለት ነው። መምጣቱን ለዮሴፍ ያበሠረው መልአክ፥

> «እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና፥ ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ» (ማቴ. 1፡21) ያለው ለዚህ ነበር።

እነዚህን ሐቆች መረዳት «የምሥራቹን ቃል» ለሌሎች እንድናካፍል ግድ ይለናል። «ወንጌል» የሚለው ቃልም ትርጉሙ ይኸው ነው። ስለ ክርስትና ከሰማኸው ነገር ጋር ስለማይሄድልህ፥ ይህንን ማንበብ እንደሚረብሽህ የታወቀ ነው። የተለመደውን አስተሳሰብ የሚቃረን ቢሆንም እንኳ፥ ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ መበርታቱ አይሻልምን? ደግሞ እኮ በመጨረሻው ልናደርጋቸው የምንችላቸው ማሻሻያዎች አይኖሩም። ለምናምነውም ሆነ ለምናደርገው ነገር ኃላፊነቱ የእኛው ይሆናል።

እባክህ ይህንን እንደማስፈራራት አድርገህ አትተርጉመው። ይልቁንም ደብዳቤዎቹን ከፍቅር ማህፀን እንደወጡ የአሳቢነት መለዮዎች አድርገህ ተመልከታቸው።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር የምሰናበትህ ታማኝ ወንድምህ ነኝ

ቴዎፍሎስ

# ቁጥር 8

ውድ ዐብደላ፥

እስካሁን የተነጋገርንባቸው በርካታ አርዕስቶች አሁን መነሣት ወዳለበት ነጥብ አድርሰውናል፡- ኢየሱስ ማነው? ነቢይ ነውን? ሐሰተኛ ነውን? እግዚአብሔር ነውን? እስቲ «ኢየሱስ ከነቢይ በላይ» የሚለውን ማዕረግ ልጠቀም!

ከተለመደው መሠረት መጀመሩ ከሁሉም እንደሚሻል እርግጠኛ ነኝ። በመሆኑም ደግመን መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን። ስለዚህም አስቀድመን ቁርአን ስለ ኢየሱስ የሚናገረውን እንመለከታለን። እንደሚከተለውም ይነበባል፥

ከድንግል ተወልዷል
(ሱራ 19፡16-35) (ከመጽሐፍ ቅዱስ ሉቃ. 1፡26-38፤ 2፡1-20)

መሲሕ ነበር (ሱራ 4፡171)። ከመጽሐፍ ቅዱስ ዮሐ. 1፡41፤ 4፡25 ና 26)። ይህ ቃል በቁርዓን ውስጥ ፍች አልተሰጠውም። ለአይሁዶችና ለክርስቲያኖች መሢሑ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ነፃ ለማውጣት የተላከ ሰው ነው።

እርሱ ከእግዚአብሔር የተላከ መንፈስ ነበር
(ሱራ 4፡171)

እርሱ የእግዚአብሔር ቃል ነበር
(ሱራ 4፡171) (ከመጽሐፍ ቅዱስ ዮሐ. 1፡1-14)

የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር አሳብ እንደሆነና ያውም የእግዚአብሔር ክፍል እንደሆነ እንረዳለን።

እርሱ ሕይወትን ፈጥሯል፤ ሕሙማንንም ፈውሷል
(ሱራ 3፡49) (ከመጽሐፍ ቅዱስ ማቴ. 11፡1-6)

እርሱ ለሰው ልጆች ሁሉ ምልክት ነው።
(ሱራ 19፡21)። (ከመጽሐፍ ቅዱስ ሉቃ. 2፡25-32)

በዚህም ሆነ በሚመጣው ዓለም እርሱ አንጸባራቂ ክብር አለው
(ሱራ 3፡45)። (ከመጽሐፍ ቅዱስ ዕብ. 1፡3፤ ቆላ. 1፡16፤ 2፡9)

እርሱ በእግዚአብሔር ወደ ሰማይ ተወስዷል
(ሱራ 4፡158)። (ከመጽሐፍ ቅዱስ የሐዋ. 1፡9-11)።

በዓለም ላይ ለመፍረድ ዳግም ይመለሳል
(ሱራ 43፡61፤ ሚሽካት 4 ገጽ 78-80)፤
(ከመጽሐፍ ቅዱስ ዮሐ. 14፡1-6፤ 5፡22፥ 25-27)

እርሱ ቅዱስ ነበር /ፒከሻል/ ወይም አለነቀፋ ነበር (ዋይ ዓሊ)
(ሱራ 19:19) (ከመጽሐፍ ቅዱስ ዕብ. 7:26)

ብዙ ሙስሊሞች ነቢያት ሁሉ ኃጢአት እንደሌለባቸው አድርገው ያምናሉ። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ቁርዓን ይህንን ይቃረናሉ። አዳም ኃጢአት ሠርቷል (ሱራ 2:36፤ 7:22-23)፤ (ከመጽሐፍ ቅዱስ ዘፍ. 3:1-19)፥ አብርሃምም እንዲሁ አድርጓል (ሱራ 26:82)፤ (ከመጽሐፍ ቅዱስ ዘፍ. 12:10-20፤ 20:1-19)፥ ሙሴ (ሱራ 28:15-16) (ከመጽሐፍ ቅዱስ ዘጸአ. 2:11-12፤ ዘሁል. 20:9-12)፥ ዮናስ (ሱራ 37:142)፤ (ከመጽሐፍ ቅዱስ ዮናስ 1:3-16)፥ ዳዊት (ሱራ 38:24-25)፤ (ከመጽሐፍ ቅዱስ 2 ሳሙ. 11:2-21፤ 12:13-14፤ መዝ. (51):3-4)፥ እንዲሁም መሐመድ (ሱራ 47:19፤ 48:1-2)። ይህ ኢየሱስን የተለየ አያደርገውምን?

ይህም እነዚህን ሁሉ ባሕርያት በራሱ የተላበሰ ሰው ሰብዕናው ወይም መለኮታዊነቱ ምን ያህል ሊሆን ይችላል? የሚለውን ጥያቄ ያስነሣል። ከእነዚህ ባሕሪያት ሁለቱ እንኳ የራሱ እንደሆኑ አድርጎ ሊመካ የሚችል አንድ ሰው ልናገኝ እንችል ይሆን? ኢየሱስን በተመለከተ ሊሰጥ የሚችለው ድምዳሜ እርሱ ከሰው የላቀ እንደሆነ ብቻ ነው። ያም መለኮታዊነት ነው!

እዚህ ጥቂት ገለጻ መስጠቱ አስፈላጊ ነው። ክርስቲያኖች አይሁዳዊያን ናቸው። እኛ አንድን አምላክ ብቻ እናመልካለን። መጽሐፍ ቅዱሳችን እንደሚያስተምረን በአንድ አምላክ እናምናለን።

«አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው»
(ዘዳ. 6:4)

«... እግዚአብሔር እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ»
(ዘጸ. 20:2 ና 3)

ኢየሱስ በዚህ መለኮታዊነት ምስል ውስጥ የቱጋ እንደሚገባ ትጠይቅ ይሆናል። ይህንን ውስብስብ መንፈሳዊ ሳብ እንዳብራራልህ ትንሽ ጊዜ ስጠኝ። እኔ አንድ ግለሰብ ብሆንም፥ ከሥጋ፥ ከነፍስና ከመንፈስ የተሠራሁ መሆኔ እርግጥ ነው። እኔ የሦስቱ አንድነት ውጤት የሆንሁ አሐድ ነኝ። ሥጋዬ ከእኔ ጋር ባይኖር እኔ፥ እኔ አይደለሁም፤ ያለ መንፈሴና ነፍሴም እንዲሁ። እስኪ ይህንን ተምሳሌት በእግዚአብሔር ባሕርይ ላይ በአክብሮት ልጠቀምበት። የእግዚአብሔር ቃል ስለ እግዚአብሔር የሚናገረው ፈጣሪና አባት እንደሆነ ነው። እንዲሁም ሰብዓዊ ሕልውና እንደተላበሰም ይናገራል (ዮሐ. 1:1-5፤ 9-14፤ ፊልጵ. 2:5-11፤ ኢሳ. 63:8፤ ሮሜ 9:5፤ ቆላ. 2:90)። ይህንንም ያደረገው የሰውን አካል ለብሶ ራሱን ለሰው ልጅ ለመግለጽና በኃጢአት ጠንቅ ከእግዚአብሔር ለተለየው ዳግም ኅብረት የምንፈጥርበትን መንገድ ለመስጠት ነው። በዚህም «ወልድ» አዳኛችን ሆነ። ይህ

የእግዚአብሔር መገለጽ ነው (2 ጢሞ. 1፡8-10)። የእግዚአብሔር መንፈስ ሰዎችን በልባቸውና በኅሊናቸው ስለ ኃጢአትና ስለ ጽድቅ በመውቀስ ወደ እውነት ይመራቸዋል (ዮሐ. 16፡7-15)። የተወሳሰቡትን የሥነ-መለኮት ቀመሮች ወደ ጎን በመተው አንዱ አምላክ ራሱን በሦስት መልኮች፥ ተግባሮች፥ ወይም ባሕርያት ለመግለጽ እንደመረጠ ብቻ ልንቀበል እንችላለን። ይኸውም በፍጥረት፥ እንደ አዳኝና መሪ ነው። እነዚህን ማዕረጎች ለራሱ እየሰጠ ራሱን በዚህ ዓይነት መንገድ ለመግለጽ መረጠ። እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚያሻው ጉዳይ መንፈሳዊንና ዘላለማዊውን እውነት በሰው አስተሳሰቦች፥ ጊዜና ቦታ በተገለጸው ቋንቋ መግለጹ እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን ነው። በተጨማሪም የእግዚአብሔር ቃል ከጥንቱ ታሪክ እስከ «አቶሚክ» ዘመን፥ ባልተማሩትና በምሁራን ዘንድ ሁሉ ግልጽ መሆን ነበረበት።

እግዚአብሔር ስለ ራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የገለጠው፥ ለትውልዶች ሁሉ አሳማኝ ሁኔታ ይህንን ያብራራል። «እግዚአብሔር» ተብሎ የተተረጎመው ቃል በዕብራይስጥ «ኤሎሄ» ወይም «ኤሎሂም» የሚለው እንደሆነ እያንዳንዱ አይሁዳዊ ያውቀዋል። የቃሉ የመጨረሻ ፊደላት «. . ሂም» የሚያመለክቱት ብዙ ቁጥርን ስለሆነ «እግዚአብሔሮች» ተብሎ ሊነበብ ይችላል። ለሙሴ በተሰጠው በዘዳግም 6፡4 ላይ የሚከተለውን እናነባለን፡-

> «ያህዌ (ጌታ) ኢሉሄኑ (አምላካችችን) ያህዌ ኤካድ (ጌታ አንድ) ወይንም አሐድ ነው።»

በኋላ እግዚአብሔር ይህንን በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል አብራርቶታል (63፡7-10)።

> «የእግዚአብሔርን ቸርነት . . . አስባለሁ . . . ኢያሱ (ኢየሱስ የሚለውን የሚተካ የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙ አዳኝ ማለት ነው) . . . እነርሱ ግን ዓመፁ ቅዱስ መንፈሱንም አስመረሩ»

ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ ከብዙ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ይህንን የገለጸው ሲሆን፥ ለዚህም የራሱ ምክንያት ይኖረዋል።

በወንጌል ውስጥ ኢየሱስ በተደጋጋሚ «የእግዚአብሔር ልጅ» ወይም «የሰው ልጅ» እየተባለ ተጠርቷል። እነዚህም በመሠረቱ ተመሳሳዮች ናቸው። ነቢዩ ዳንኤል የጻፈውን ልብ በል፡-

> «በሌሊት ራእይ አየሁ! እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ . . . ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙአት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው! ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው! መንግሥቱም የማይጠፋ ነው»
>
> (ዳን. 7፡13-14)

«ልጅ የሚለው ቃል ከማርያም ጋር የሥጋ ግንኙነት በመፈጸም አንድያ ልጅን የማግኘትን አሳብ የሚያንጸባርቅ አይደለም፥ ይልቁንም በያህዌና በኢያሱ፥ በእግዚአብሔርና በኢየሱስ መካከል ያለውን የተለየ ዝምድና የሚያሳይ ነው። በዘር ሐረግም ሆነ በሌላ በማንኛውም ረገድ ወንድ ልጅ ከአባቱ ጋር እጅግ የቀረበ ነው። ሁለቱም አንድ ዓይነት ናቸው።

«የመንገድ ልጅ» እንደሚለው ሐረግ ዓይነት አነጋገር ሆኖ ሊታይ ይችላል። ይህ ሐረግ እንደሰማሁት ከሆነ፥ መንገደኛ ለሚለው ቃል የተሰጠ የዐረብኛ ቃል ትርጉም ነው። ሐረጉ በመንገዱና በመንገደኛው መካከል ያለውን ዝምድና ለማሳየት የቆመ ነው። «አንዲያ ልጅ» የሚሉት የሚያምታቱ ቃላት በአንድ የጥንት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንደሚለው «ብቸኛ ልጅ» የሚል ትርጉም ይሰጣሉ። «የእግዚአብሔር ልጅ» «የመምጣቱ አስፈላጊነት» በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ተብራርቷል። እንደኛውም ገጽታ:-

«እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና»
(2 ቆሮ. 5:19)

የሚለው ነው። በዚህ አሳብ ላይ ኢየሱስ የማያሻማ መልስ ሰጥቷል፤

«እኔ መንገድ፥ እውነትና ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም»
(ዮሐ. 14:6)

ይህ ሁሉ የሚያሰናክልህ ባይሆን እንኳ፥ እንግዳ አሳብ እንደሚሆንብህ የታወቀ ነው። ስሜትህ ስሜቴ ነው ብለህ ታምነኝ ይሆን? ደግሞም ይህ ሁሉን ቻይ ከሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተገለጸና ብዙ መረጃዎች ያለው እውነት እንደሆነ ተረድቷል። ታዲያ ይህን እውነት እንቃወመውን? እኔ እንደ ሰባኪ ሆኜ ለመቅረብ አልፈልግም፤ ጻሩ ግን የወንጌሉን እውነት በተመለከተ፥ እንድታነበው ብቻ ሳይሆን፥ እንድታረጋግጠው፥ እንድትመረምረውና ለሕይወትህ የሚበጅ ውሳኔ እንድትወስን ላደፋፍርህ እወዳለሁ።

ታማኝ ጓደኛህ

ቴዎፍሎስ

## ቁጥር 9

ውድ ዐብደላ

ባለፈው ለጻፍሁልህ ደብዳቤ ስለላክህልኝ መልስ በጣም አመሰግናለሁ። በውስጠ, ጥቂት ስጋቶች ቢኖሩኝም ቅሉ ለእግዚአብሔር ካለህ ሁለንተናዊ መገዛት በተጨማሪ በእምነት ጉዳዮች ላይ ትክክለኛ የሆነን አስተሳሰብ አስፈላጊነት እንደምትቀበል አረጋግጠህልኛል። በዚህ የውሸትና የማታለል ዓለም ላይ በሁለቱም እግሮች ጸን‐ መቆም እንደሚያሻ አጥብቄ አምናለሁ። ምናልባት አንደኛውን እግር ቅንና ትክክለኛ በሆነው አሳብ ልመስለው። ይህም ቅን አሳብ ለማንኛውም ዓይነት የሃይማኖ‐ ፅንሰ-ሐሳብ ክፍት ሆኖ፣ ዳሩ ግን ጠበቅ ያለ ሊሆን ይገባል። እንዲሁም ራሱን እውነ‐ አድርጎ የሚያስተዋውቀውን ሁሉ መረጃዎችን፣ ማጣቀሻዎችንና ከሁሉም በላይ መለኮታዊ ምንጭ እንዳለው የሚጠቁሙ ማስረጃዎችን እያገላበጠ ለመፈተን ት‐ መሆን አለበት። ሌላው እግር ደግሞ ሁሉን ቻይ ለሆነው እግዚአብሔር ባልተከፈለ ልብ፣ በንጹሕ አምልኮ፣ በፍቅርና ሁኔታ በማይወስነው መታዘዝ ራስን መስጠት ይወክላል።

ከእነዚህ ከሁለቱ እግሮች በአንዱ ብቻ የሚቆም ሰው፣ ለመውደቅ የተንገዳገደ፣ በማይሆን የስሜት መዋዠቅ የተዋከበ አክራሪ ሃይማኖተኛ፣ ወይም ከራሱ «ጎራ» ከመጡት የሃይማኖት መሪዎች ብቻ የሚማረውን ሳይመረምር የሚያምን ተራ ሰ‐ ነው። አሊያም ከፈጣሪው ጋር ምንም የግል ግንኙነት ሳያደርግ፣ እንዲሁ ብ‐ እግዚአብሔርን በምድራዊ አመለካከቱ ልበ-ቀዝቃዛ ግን የሥነ-መለኮት ምሑር ሊሆን ይችላል።

አዳዲስ የሃይማኖት አሳቦች በሚያጋጥሙን ጊዜ፣ በመጀመሪያ ደረ‐ መለኮታዊነቱን ሊያጸድቁ፣ ወይም ውድቅ ሊያደርጉ የሚችሉትን መረጃዎ‐ በጥንቃቄ እየመረመርን ከግለኝነት ስሜት ነፃ በሆነው በእውቀት «እግራችን» ባገኘነ‐ እውነት ላይ እንቆማለን። አንድ ጊዜ እውነትነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ደግሞ ግላ‐ ወደሆነው ከልባችን ጋር ወደተያያዘው «እግር» ያለችግር እንሻገራለን። ይህንን‐ የምናደርገው ተገዥነታችንን በአምልኮ ለመለማመድና ራሳችንን ለእግዚአብሔ‐ አገልግሎት ለማቅረብ ነው።

እስካሁን ባሉት ደብዳቤዎቼ ሁሉ ከግለኝነት ስሜት ነፃ በሆነው «እግር» እንደቆምህ አምናለሁ። አሁን በዚያው ላይ ጥቂት ልትሰነብት እና የኢየሱስን ስቅለት‐ ሞት ከእኔ ጋር ልትመለከት ትችላለህን? ባለፈው ደብዳቤ ከተመለከትነው ከውስብስ‐ የኢየሱስ መለኮታዊነት ጉዳይ በተጨማሪ፣ መስቀሉም በክርስቲያኖችና በሙስሊሞ‐ መካከል አለመስማማትን በከፍተኛ ደረጃ የፈጠረ ርዕስ ነው። ስለ እርሱም ለመወያየ‐ መበርታት ያሻል። እዚህ ላይ ይህ መቼም አንተን ለመጉዳት ወይም ክርክሩን ለማሸነ‐

ተደረገ እንዳልሆነ ትገነዘባለህ። የዚህ ክስተትና አስፈላጊነቱ ምናልባት ሳትረዳ ምትቀርበት አጋጣሚ ከተፈጠረ፥ በጣም ልዩ የሆነው ጓደኝነታችን ለአደጋ ንዳይጋለጥብኝ ብዬ እፈራለሁ። መቼም የእኛ ጓደኝነት ከእግዚአብሔር ፍቅር የተነሣ ‹አደገኛ› ነጥቦችን እንኳ ስለማይዘልል በጣም ልዩ ነው።

ሁለታችንም «በየመጻሕፍታችን» ውስጥ ያሉትን ተጻራሪ መግለጫዎች ናውቃለን። ቁርዓን በግልጽ የሚከተለውን ይዘግባል፡- «. . . እነርሱ (ማለትም ይሁዶች) ኢየሱስን አልገደሉትም! አልሰቀሉትምም . . . እንደ እውነቱ ከሆነ ልገደሉትም!» ዘገባው ክስተቱ የተፈጸመ እንደመሰላቸውና እርሱን ግን ግዚአብሔር ወደ ራሱ እንደወሰደው ይገልጻል። (ሱራ 4፡157)። ከዚህ በተቃራኒ ኢየሱስን ስቅለትና ሞት በወንጌል ውስጥ እጅግ ከፍ ያለ ሥፍራ ይዟል! በብሉይ ኪዳን፥ እና በኢየሱስ ሞትና ሕይወት ፍጻሜአቸውን ያገኙ ትንቢቶችም ውስጥ ቸል ሊባል የማይችል ሆኖ ተቀምጧል። መቼም ሁለቱም ዘገባዎች እውነተኛ ሊሆኑ ንደማይችሉ ግልጽ ነው። እንደተለመደው ምሽጎቻችን ውስጥ ገብተን ከመቃኮስ ልቅ፥ እንደገና ከግላዊ ስሜት ነፃ የሆነውን «እግር» እንጠቀምና፥ አንደኛውንም ወይም ሌላኛውን አቋም የሚደግፉ፥ ወይም የሚቃወሙ መረጃዎችን እንመርምር።

ባለፉት ደብዳቤዎቼ (2 እና 4) በዚህ ጉዳይ ላይ የቁርዓን ምስክርነት ጨምሮ መጽሐፍ ቅዱስን ተአማኒነት በጉልህ እንዳሳየሁህ ታስታውሳለህ። ስለተፈጸሙት ትንቢቶች፥ የዓይን ምስክሮች ዘገባ፥ ዘመናዊ የታሪክ ዘገባዎችንና የከርሰ-ምድር መረጃዎችን ጠቅሻለሁ። እነዚህ ሁሉ ተቃውሞ የኢየሱስን መሰቀልና መሞት ሚያመለክቱትን በርካታ ዘገባዎች በመደገፍ የሚናገሩ ናቸው። ይህ ሁሉ ተቃውሞ ደረሰበት፥ ምናልባት አሳቡን ባልተረዳንለት ከአንድ ሰው መግለጫ የተነሣ ነውን? መግለጫው ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደለመዱት ዓይነት በመረጃ ልተደገፈ መሆኑ ደግሞ ነገሩን የበለጠ ያወሳስበዋል።

በዚህ ነጥብ ላይ ድጋፍ ሰጪ መረጃዎቻችንን ለመድገም ብፈተንም፥ በጥሩ ማስታወስ ችሎታህ መተማመኑን መርጫለሁ። በተመሳሳይ መልኩ ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅና ይቅርታን ለማግኘት መሠረታዊና አስፈላጊ ስለሆነው ስለ በደል መሥዋዕትና መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ትምህርትና ኢየሱስም ያን መሥዋዕት መሆን ከመጀመሪያ እንዴት እንደተመረጠ፥ በመጥምቁ ዮሐንስ ቋንቋ «የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ» (ዮሐ. 1፡29) እንደሆነም ለማሳየት ዳድቶኝ ነበር። ይህን ጉዳይ ለመረዳት ፍላጎት ቢኖርህ በሌላ ደብዳቤ እጽፍልሃለሁ። ይልቅስ እግዚአብሔር መስቀሉ ሊፈጸም ለሚፈልገው ነጥብ እንደ ምሳሌ ሊሆን የሚችለውን ክስተት ጠቀም። ሳሙኤል ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት የኖረ የነጮች ልዑል ነበር። የርሱም ከዝቦች ከቱርኮች ጋር በማያቋርጥ ጦርነት ነበሩ። አንድ ጊዜ በአንዲት የቱርክ ከተማ ይ ከበባ አደረገ። እንደተለመደው እናቱም ከካምፑ ውስጥ ከእርሱ ጋር ነበረች።

አንድ ሌሊት ድንገተኛ ጥቃት ለመሰንዘር አቀደ፤ ዳሩ ግን የጠላት ጦር ነቅቶ ይጠብቀው ነበር። ምሥጢሩ በከዳተኞች ባከናበት ስለነበር በውጊያው ድል ሆነ። በታላቅ ቁጣም ምስጢሩን ለጠላት የሚያቀብለው ሰው ከተገኘ በመቶ ጅራፍ ግርፋት እንደሚቀጣ ሳሙኤል አስታወቀ። እንደገናም በጥልቅ ምስጢር ሌላ ድንገተኛ ጥቃት ታቀደ። ውጤቱ ግን ያው ሆነ። ይሁንና ወሬ አቀባዩ ተያዘ-የሳሙኤል እናት ነበረች።

ለሦስት ቀናትና ሌሊት ሳሙኤል ራሱን በድንኳኑ ውስጥ ሸሸገ። ምን ያድርግ? እናቱን ቢያድናት፥ እርሱ ፍርደ ገምድል እንደሆነ ሁሉም ይናገራሉ። ቢቀጣት ደግሞ ሁሉም፥ «ሳሙኤልን እዩት! ለገዛ እናቱ እንኳ ርኅራኄ የለውም!» ማለታቸው አይቀርም። ከብዙ ቆይታም በኋላ ከተሸሸገበት ድንኳን ብቅ አለ። ጦሩም በጉጉት ተሰባሰበ። ኮስተር ባለ ሁኔታም ለሕዝቡ የሚከተለውን ተናገረ፡- «ከወሬ ቅብብሎሹ የተነሣ ሁለት ውጊያዎችን አጥተናል። ብዙ ሰዎችም ተገድለውብናል። ስለዚህም ይቅርታ የሚባል ነገር የለም። ጥፋቱ ስለተፈጸመ፥ በሕጊ መሠረት የመቶ ጅራፍ ግርፋቱ መከናወን አለበት። ጽድቅና ፍርድ መተጓጎል የለባቸውም።»

እናቱም ወደ መግረፊያው ቦታ ተወሰደች። ፊቷ ገርጥቶ በፍርሃት ትንቀጠቀጥ ጀመር። ገራፊውም መግረፊያውን አነሣ፤ ዳሩ ግን የመጀመሪያው ግርፋት ከማረፉ በፊት ሳሙኤል ጮኸ፥ «ቆየኝ! ይህች እናቴ ነች፤ እኔም ከደምዋና ከሥጋዋ የወጣሁ ነኝ። እኔ ቅጣቱን እቀበልላታለሁ» አለ። ልብሱን አውልቆ ወደ መግረፊያው ቦታ በመግባት፥ «ገራፊ ሆይ፤ ካለፈው ተገራፊ ላይ ከተፈጸመው በታች ስንዝርህን ለማቅለል እንዳትደፍር። ኃላፊነትህን ተወጣ። በል ቀጥል!» ራሱን ስቶ እስኪወድቅ ድረስ የግርፋት ውርጅብኝ ወረደበት። ዳሩ ግን ማንም ባልጠበቀው ሁኔታ ሊተርፍ ችሏል።

ይህ ምናልባት በታሪክ ውስጥ ከተመዘገበው ከማንኛውም ክስተት በላይ ከኢየሱስ ሁኔታ ጋር ሊዛመድ ይችላል። እርሱ በአካል ውስጥ ያደረ እግዚአብሔር ነበር። ጻድቅ ፍርድም መፍረድ ነበረበት። ዳሩ ግን በፍጹም ፍቅሩ የእኛን፥ የእኔንና ያንተን ኃጢአት በራሱ ላይ በማኖር፥ የዚህ ውጤት የሆነውን ጭካኔ የተሞላበትን፥ ነገር ግን ፍትሐዊውን ሥቃይ በመስቀል ላይ ተቀብሏል። ከሁሉ የባሰው ግን ያስከፋው ሥጋዊው መከራ ሳይሆን እጅግ ንጹሕና ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር ራሱ የኃጢአታችንን መርገም መሸከሙ እንደሆነ እናውቃለን።

ጽድቅና ፍቅር በኢየሱስ መስቀል ላይ ተገናኙ።

> «እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፤ በደላቸውን (በእግዚአብሔር ሕግ ላይ) አይቆጥርባቸውም ነበር»
>
> (2ኛ ቆሮ. 5፡19)

ይህ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተፈጽሟል። ይህ የኃጢአት መሥዋዕት በማንኛውም ወቅት ለሰዎች ሁሉ ብቁ ነው። እርሱም ለእኛ የማይገባውና የእግዚአብሔር ጸጋ፥ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ሆኖም አንድ ስጦታ የእኔ ሊሆን የሚችለው ስቀበለውና ስንከባከበው ነው።

በልቤ ኃጢአቴን ሁሉ በንስሓ ጸሎት ወደ እርሱ ካቀረብሁ፥ ከኃጢአቴ እንጻለሁ፥

«በደላቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና»
(ኤር. 31:34)

«ኃጢአታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል»
(ሚክ. 7:19)

«ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፥ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ»
(መዝ. (103):12)

«በኃጢአታችን ብንናዘዝ፥ ኃጢአታችን ይቅር ሊለን፥ ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው»
(1ኛ ዮሐ. 1:9)

ኢየሱስ ማን እንደሆነና ምን እንዳደረገ ከተገነዘበ በኋላ፥ እና እኛ በገዛ ፈቃዳችን ሳቢያ ኢየሱስን በመስቀል ላይ እንደቸነከርነው እያወቀ ቁርጥ ጸጸት ሳያደርግ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረት በቀላሉ ለመጠየቅ እንደማይደፍር እርግጠኛ ነኝ። ደግሞስ ይህን ከተገነዘበ በኋላ ሰው እንዴት ኃጢአት በልቡ ያስተናግዳል? እርግጥ ነው ልንደናቀፍ እንችላለን። ልንወድቅም እንችላለን። ጻሩ ግን እግዚአብሔርን የሚያስቀይሙ ተግባራትን አልመንና አቅደን አንፈጽምም።

ባለፈው ክፍለ-ዘመን አንድ አውስትራሊያዊ ሠዓሊ የስቅለትን ምስል እንዲሠራ ታዝዞ ነበር። እርሱም በአእምሮው ካለው አሳብ ጋር የሚስማሙ የተወሰኑ ሞዴሎችን መርጦ ሥሏል። ነገር ግን ለአንዲት በዓይኑ ኅሊናው ውስጥ ለነበረች ወጣት ሴት ብቻ የሚሆን ቀለም ሳይቀባ ክፍት ቦታ አስቀረ። በከተማም ውስጥ ሲመላለስ ሳለ በአንዲት ከጂፕሲዎች ወገን በሆነች ሴት ተማረከ። ለሥነ-ጥበብ ሥራው የጎደለችው ሰው እርሷ ነበረች። እርሷም የምስሉ ሞዴል ሆና ለማገልገል ተስማማች። ክፍያውም ተወሰነ እና የሥዕል ሥራውን ወደሚያከናውንበት እስቱድዮ ወሰዳት። ጂፕሲዋን የራስዋን ሥዕል በማስተዋል ከተመለከተች በኋላ፥

«ያ በመስቀል ላይ ያለው ሰው ይህን ያህል ቅጣት የተቀበለው እስከፊ ወንጀለኛ ቢሆን ነው» በማለት አስተያየቷን ሰነዘረች።

ሠዓሊውም «አይደለም» በማለት መለሰላት፥ «እንዲያውም እርሱ ኃጢአት ያልነካው ነው!» አለ።

ጂፕሲዋም «እንዲህ ከሆነ ታዲያ እንዴት ሊገድሉት ቻሉ?» ስትል ጠየቀች።

«እርግጥ እርሱ የሞተው ሰዎች ለሠሩት ኃጢአት ነው» ሲል አብራራ የስም ክርስቲያን የነበረው ሠዓሊ።

«ለአንተም ጭምር ነው?» ስትል ጠየቀችው።

ሠዓሊው አሁን አሰብ በማድረግ «አዎን» አለ። «እንግዲህ እርሱን አጥብቀህ ትወደዋለህ ማለት ነው» አለችው ምንም የማታውቀው ጂፕሲ። ኢየሱስን የማይወድ የነበረው ሠዓሊ እነዚህ ቃላት ልቡን ነኩት። በዚህም አጋጣሚ ሕይወቱ በኢየሱስ ሊለወጥ ቻለ። ብዙ እውነተኛ ክርስቲያኖች በዚህ ሂደት ውስጥ ያለፉ ይመስለኛል። በመጀመሪያ ስለ ራሳችን ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት እንመጻደቅ ነበር። አሊያም ጽድቅን ስላማጣታችን እናስብ ነበር። የእግዚአብሕርን መንገድ በመከተል ይቅርታንና ነፃነትን ባገኘን ጊዜ፥ ለኢየሱስ ያለን ፍቅር ይመጥቃል። በዚህም ዓይነት በሁለቱ እግሮቻችን ለመቆም እንጀምራለን።

የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት መቃወም አዲስ አሳብ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱሳችንም ውስጥ የሚከተለውን ጥቅስ እናገኛለን:-

> «የመስቀሉም ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፤ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና»
>
> (1 ቆሮ. 1:18)

ይህ ጥቆማ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። መስቀሉ የሰው ልጆችን በሁለት ጎራዎች ይከፍላቸዋል። እነዚህ የሚጠፉትና ከኩነኔ ነፃ የሆኑት ናቸው። ይህም ፍርድ እግዚአብሔር በኢየሱስ በኩል የሚሰጠውን ይቅርታ ቸል ለሚሉ ወንዶችና ሴቶች ሁሉ የማይቀር ነው። ተቀባይነትን ያጣ ይቅርታ፥ በከንቱ የባከነ ይቅርታ ነው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌላ ሥፍራ ደግሞ ስለ መስቀሉ ዕንቅፋት እናነባለን (ገላ. 5:11)። ለመሆኑ የኢየሱስ መስቀል ዕንቅፋትና ሞኝነት የሆነው የቱ ላይ ነው? የምንባቡ ክፍል የማያሻማ መልስ ይሰጠናል። የመስቀሉ ቃል የሰው ልጅ ለኃጢአት ማካካሻ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ጥረቶች ሁሉ ከንቱ መሆናቸውን እግዚአብሔር ያወጀበት ነው። የመስቀሉ ቃል ሰው በራሱ ሙሉ ለሙሉ ደካማ እንደሆነና ወደ ዘላለማዊ ቤታችን ለመድረስ እግዚአብሔር ያዘጋጀው ድልድይ ብቸኛ መታመኛችን እንደሆነ ያስታወቀበት ነው።

እግዚአብሔር ለእኛ፥ ለፍጡራኑ ሲል እራሱን ዝቅ ያደረገበት መንገድ ይህ ነው። ራሳችን ማድረግ የማንችለውን ነገርም ያደርግልናል።

> «የሥጋንም ሰውነት በመግፈፍ፥ በክርስቶስ መገረዝ፥ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ፤ በጥምቀትም ከርሱ ጋር ተቀብራችሁ፤ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ

ጋር ተነሣችሁ። እናንተም በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ፥ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ፥ በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ፤ በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፤ እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል፤ አለቅነትንና ሥልጣንን ገፎ፥ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው»

(ቆላ. 2፡11-15)

ውድ ዐብደላ፥ ይህን መልእክት በመጀመሪያ በአእምሮህ፥ ቀጥሎም በልብህ ለመመርመር ጊዜ ትወስዳለህ? ምንም ዓይነት ውሳኔ ብትወስን፥ ውሳኔህ በሕይወት እና በሞት መካከል መሆኑን ልብ ማለት አለብህ!!! ይህን ጥብቅ ማሳሰቢያ ሙሴ ለሕዝበ-እሥራኤል ባቀረበው ጥያቄ ባጠቃልለው ሳይሻል አይቀርም፡-

«በፊታችሁም ሕይወትንና ሞትን፥ በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ፤ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ»

(ዘዳ. 30፡19)

ታማኝ ጓደኛህ
ቴዎፍሎስ

# ቁጥር 10

ውድ ዐብደላ፥

ምላሽህን በብዙ ምስጋና ተቀብያለሁ። የራሴንም መልስ እስከምልክልህ ጊዜ ድረስ ምንም የአእምሮ ዕረፍት አላገኘሁም። ምክንያቱም በሐሳብ አለመግባባት ሹልክ ብሎ በመግባቱ ነው። ያንንም አሁኑኑ ግልጽ ለማድረግ እሞክራለሁ።

«ወደ ክርስትና ቀይረህ እንድትገባ» እፈልግ እንደሆነ ጠይቀኸኛል። እስቲ ይህን በስሕተት መንገዶች ሊተረጎም የሚችለውን ጥያቄ ለመመለስ ልሞክር። ይልቁንም በዚህ ሳምንት፥ አንድ ምሽት ከሁለት ወጣት ባለትዳሮች ጋር ማሳለፌ የሚያስደስት ነገር ነው። የአንደኛዋ ባልና የሁለተኛው ሚስት ከእስልምና የመጡ ሲሆኑ፥ የትዳር ጓደኞቻቸው ግን በክርስቲያን ማኅበረሰብ ውስጥ ያደጉ ነበሩ። አንደኛው ወጣት «እንደተለወጠ» አጫውቶኛል። ለማለት የፈለገው ሃይማኖቱን እንደቀየረ ነው። «ክርስቲያን ወደ መሆን ተለውጧል»። ይህ ሰው ምን ማለቱ ነው? አንተስ ምን እያልህ ነው?

ምናልባት አንዱን ሃይማኖት ለቀህ ወደ ሌላው እንድትገባ የምፈልግ ይመስልህ ይሆናል። ወደ ካባ ዞሮ በመጸለይ ፈንታ ፊትህን ወደ ኢየሩሳሌም ታዞራለህ። በምትጸልይበት ጊዜ በግንባርህ በመደፋት ፈንታ፥ ትቆማለህ፤ ወይም ትቀመጣለህ። የዓሣማ ሥጋ ልትበላ ትችላለህ፤ ወዘተ. አገላለጼን ሲበዛ ሥዕላዊ አድርጌው ይሆናል፥ ግና አንተ ልለው የፈለግሁትን ትረዳኛለህ።

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት «መለወጥ» ማለት መቀየር ወይም መመለስ ማለት ነው። መለወጥ የሚችል መኪና ከግልጽነት ወደ ሽፍንነት የሚቀየር መኪና ነው። እስቲ በመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃቀም መሠረት ይህ ቃል ምን እንደሚመስል እንመልከት፡-

> «አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፤ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ። ከፊትህ አትጣለኝ፤ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ . . . ለሕግ ተላላፊዎች መንገድህን አስተምራለሁ፤ ኃጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሳሉ»
>
> (መዝ. (51)፡ 10-13)

ከኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ አንዱ የነበረው ሐዋርያው ጴጥሮስ ለሰዎች በተናገረ ጊዜ እንዲህ ብሏል፡-

> «ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሓ ግቡ፤ ተመለሱም»
>
> (የሐዋ. 3፡19)

በኢየሱስ ደቀመዛሙርት በመንግሥተ-ሰማይ ከሁሉ ታላቅ የሚሆነው ማን እንደሆነ በጠየቁት ጊዜ፥

«ካልተመለሳችሁ፥ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ መንግሥተ-ሰማያት ከቶ አትገቡም»

(ማቴ. 18፡3)

ሲል መልሷል። በሌላ ሥፍራም የሚከተለውን እናነባለን፡-

« . . . ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት የሚመልሰው፥ ነፍሱን ከሞት እንዲያድን . . . ይወቅ»

(ያዕ. 5፡20)

የ1954ቱን የድሮ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንደተጠቀምሁ ሳትረዳ አትቀርም። ብዙዎቹ አዲስ ትርጉሞች «መለወጥ» የሚለውን ቃል «መቀየር» ወይም «መመለስ» ብለው ያቀርባሉ።

ልብ ማለት የሚያሻን ከዚህ በላይ የቀረቡት ጥቅሶች በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በተጻፉበት ጊዜ፥ ሰው የሚቀላቀልበት ቤተክርስቲያን ገና ያልተመሠረተ መሆኑን ነው። ይህን እንደጻፉት ሁሉ፥ ምናልባት አንባቢዎችም ሁሉ አይሁዶች ይሆናሉ። መለወጥ ከኃጢአት፥ ወይም ከስሕተት ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው። መለወጥ የኃጢአትን ይቅርታና በዚያውም ለመንግሥተ ሰማያት መዘጋጀት ያካትታል። የአእምሮና የልብ መታደስን (ሮሜ. 12፡1-2)፥ የዝንባሌዎችንና የአኗኗር ዘይቤዎችን፥ የፍላጎታችንና የፈቃዳችንን ለውጥ ያስከትላል። ከመለኮታዊ መለኪያ በአንጻር ሲታይ፥ በሰው ፍላጎት፥ መሻት፥ ወይም ችሎታ የሚሆን አይደለም። ቀድሞ ከፍተኛ ሥፍራ የምንሰጣቸው የነበሩ ነገሮችና ሁኔታዎች አሁን ትርጉም-የለሽ ይሆኑብንና እግዚአብሔር በሚወድበት ልክ ኃጢአትንም ይጠላል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ እርሱ ይበልጥ እየተጠጋ ይሄዳል። ቀድሞ ከተለመደ የግዴታ ተግባር የነበረው ጸሎት፥ አሁን መንፈሳዊ እስትንፋስ ይሆናል። የእግዚአብሔርን ዓላማ፡- ለሰው ሕይወት፥ ለቤተሰብ ግንኙነትና ለዓለሙ በሞላ ምን እንደሆነ ማወቁ ራሱ ትልቅ ደስታ የሚሰጥ ነው።

ይህ በእግዚአብሔር በውስጡ ይቀሰቀሳል! በእኔ እሺታ ይረጋገጣል! በፈቃዱ ተግባራዊ ይሆናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን የባዕድ አምላክ ቁራኛ በነበሩት በአቴና ሰዎች መካከል ሲያውጅ ሳለ፥ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

«እግዚአብሔር አሁን በየቦታው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል! ቀን ቀጥሮአልና፥ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው»

(የሐዋ. 17፡30፡31)

ለዚህ ጉዳይ ቅድመ-ሁኔታው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር። የርሱ ፈቃድ ምንድነው?

«. . . ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ፥ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል»

(2 ጴጥ. 3፡9)

«ሁሉ» የሚለው ቃል አንተንና እኔንም ያጠቃልላል። እምነት በፈቃድ በኩል ምላሽ ይሰጣል። እግዚአብሔር እንዳደረገው የሚፈልግብኝን ነገር ለማድረግ እፈልጋለሁ። ስለሆነም ንስሓ በመግባት ተለውጫለሁ።

በበኩሌ፥ ይህ የሆነው ደረጃ በደረጃ ነው። እንደምገምተው፥ በዕድገቴ ወቅት ምንም ዓይነት የሃይማኖት መረዳት አልነበረኝም። ወደ ጎልማሳነት መሸጋገር ላይ ሳለሁ፥ እግዚአብሔር በቀውጢ ሁኔታ ውስጥ አስቀመጠኝ። ዓለምን በማጤን ላይ ሳለሁ በማጉያ መነጽርም ሆነ የሩቁን አቅርቦ በሚያሳይ መሣሪያ ሊታይ የሚችለውን የሕዋው ሥርዓት በመመልከት አንድ ከአእምሮ በላይ ተብሎ የሚጠራ ነገር እንዳለ ለመረዳት ችያለሁ። ይህም በተፈጥሮ ውስጥ ራሱን የሚገልጸው እግዚአብሔር ነበር። ያለምንም ሰው ጣልቃ-ገብነት ሕይወቴ ዓላማ ሊኖረው እንደሚገባ ወሰንሁ። ዘላለማዊነት ሊኖር እንደሚገባም አስተዋልሁ። ስለሆነም ከአካላችን በተቃራኒ፥ እውነተኛው «እኔነቴ» ሕያው መሆን እንዳለበት ታወቀኝ። ከመጽሐፍ ቅዱስ እስከተዋወቅ ድረስ ዓመታት አለፉ። ትንቢቶቹንና ፍጻሜአቸውን በተረዳሁ ጊዜ የተደረሰው መለኮታዊ ኃይል እንደሆነና መለኮታዊ ሥልጣን እንዳለው ተገነዘብሁ። «የምሥራቹን ቃል» በሰማሁ ጊዜ በተከታይነቴ ለመቀበል የምችልበትን መሠረት ስለጣለልኝ ይህ ትልቅ እርምጃ ነበር። ወደኋላ መለስ ብዬ ሳስበው፥ እግዚአብሔር በመንገዴ ሁሉ ለዚህ እያዘጋጀኝ እንደነበር ግልጽ ሆነልኝ። የቀረው ምላሽ የምሰጥበት የራሴ ተራ ነበርና ለጥሪው አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት መረጥሁ።

በዚህም ጊዜ ንስሓ፥ አዳዲስ ግንዛቤዎች (ከእግዚአብሔር ቃል)፥ እንዲሁም ሁለንተናዊ የሆነ አዲስ ሕይወት ተከተለ። አንድ ያነበብኩትን ነጥብ ልብ በልልኝ፡-

«ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ፥ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን (እግዚአብሔር) ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው»

(1 ዮሐ. 1፡8-9)

ከዚህ ውስጥ የእግዚአብሔርን ታማኝነት እረዳለሁ። ደግሞም ግልጽ የሆነ የመነሾና የውጤት ሕግ አለ። በኃጢአቴ ተጸጽቼ በመናዘዝ ንስሓ ከገባሁ፥ በእግዚአብሔር ምሕረት ላይ ሙሉ ለሙሉ መደገፍ እችላለሁ። ይህ ከሆነ ብዙ ዓመታት ቢያልፍም፥ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ተስፋ ቃሎቹ ተአማኒነት በእርግጠኝነት ለመመስከር እችላለሁ። እስቲ ከእነዚህ የተስፋ ቃሎች አንዱን ላካፍልህ። ኢየሱስ ራሱ «እረኛ» እንደሆነ ሲናገር የሚከተለውን ብሎአል፡-

«በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔም አውቃቸዋለሁ፤ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘላለምን ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘላለምም አይጠፉም»

(የሐ. 10፡27-28)

አየህ፥ ይህ የሚያጠራጥር ተስፋ አይደለም። ስለዚህ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል አምናለሁ።

ምርጫው የእኔ እንደሆነ የአንተም ነው። የእግዚአብሔርን መንገድ ለመምረጥ ብትፈልግ፥ እንደ እኔው ሁሉ በእግዝአብሔር የተስፋ ቃሎች ላይ ለመደገፍ ትችላለህ። በእርግጥ ይህ የማያስደስቱ ውጤቶች ይኖሩታል። ድርጊቶችህን በማይረዱ ሰዎች ልትናቅ፥ እንዲያውም መሳለቂያም ልትሆን ትችላለህ። ቢሆንስ ያን ያህል የሚያስጨንቅ ነገር ነውን?

መልካም እንድንሆንና እንድናደርግ ምርጫው አስቀድሞ እንደተሰጠን በነቃ መንፈስ ስንረዳ፥ እንደ እውነቱ ከሆነ ምርጫው «ቁልቁል» እንደሆነ በቁጭት እንገነዘባለን። ስለዚህም ማድረግ የምንችለው ነገር ቢኖር፥ ከኃጢአተኛው ተፈጥሮአችን፥ ወደ እግዚአብሔር ምሕረት መጮህ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ይህንን የምናደርግበትን ጊዜ በናፍቆት እየተጠባባቀ ነው። ምክንያቱም የእኛ ውድቀት ለእርሱ ጥሩ አጋጣሚ ሲሆን፥ ማብቂአችንም ለእርሱ ጅማሬው ነውና። በእግዚአብሔር ጸጋ ይህንን የመቀበልና በገዛ ብቃታችን፥ ወይም በሰው ቃል መደገፍን የማቆም ምርጫ ስላለን፥ እጅግ ደስ ይለኛል። እግዚአብሔር ይህንን ዕድል ባይሰጠን ኖሮ እንደማሽኖች በሆንን ነበር። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መጠበቅ እንችል ነበር፤ ልባችን ተሳትፎ አይኖረውም እንጂ። እግዚአብሔር ግን ልባችን ለፍቅሩ ምላሽ እንዲሰጥ ይፈልጋል። ይህም በዚህ «ዓለም» ላይ በብዙ ሰዎች ዘንድ የማይታወቀውን ግንኙነት ይፈጥራል። ይህም ከባርነት ደረጃ ወደ ልጅነት ማዕረግ ያሸጋግረናል።

ሁሉን ቻይ የሆነውን እግዚአብሔርን ሳከብረው፥ ሳመልከውና በሙሉ ልቤ ሳገለግለው፥ እርሱ እንደ ልጁ ስለተቀበለኝ (1 ዮሐ. 3፡1-3)፥ አልፈራውም ከዚህም በላይ፡-

> «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት፥ እንደ አሳቡም ለተጠሩት፥ ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን። ... እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? ለገዛ ልጁ ያልራራለት፥ ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው፥ ያው ከእርሱ ጋር ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም? እግዚአብሔር የመረጣቸውንም ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤ የሚኮንንስ ማነው? የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?

... በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥ ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን፥ በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ቃል ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ»

(ሮሜ. 8፡28-39)

በአሳብ አለመግባባትን ሊያስከትሉ የሚቻሉትን ቃላት ግልጽ ለማድረግ ከሞከርሁ በኋላ፥ አሁን ጥያቄውን አጠቃልዬ ብመልሰው አይሻልምን?

አዎን፥ «እንድትቀየር» እፈልጋለሁ! እግዚአብሔር ያዘጋጀልህን ስጦታ በነፃ ለመቀበል፥ እንዲህ በእውነትና በትጋት ለምትፈጽማቸው ሥርዓቶች ስትመለስ ለማየት እጓጓለሁ። ምንም እንኳ ለጊዜው ሁኔታዎች አስቸጋሪ ገጽታ ቢያሳዩም፥ ኃጢአቶችህ ተሰርየውልህ፥ አንተም ደስታና ተስፋ ባለበት ሕይወት ውስጥ አዲስ ዓላማና ልብ ይዘህ ላይህ እናፍቃለሁ። በመጨረሻውም ቀን በዘላለም ክብር በጌታ እግሮች ሥር አብረን እንድንገናኝ እመኛለሁ!

ታማኝ ጓደኛህ

ቴዎፍሎስ።